# የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ፎክሎር

*በ ፍሬሕይወት ባዩ* [37]

## Abstract

The focus of this study is to show the relics used by the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church (EOTC) in terms of religious folklore. Two churches from Addis Ababa Diocese and two churches from Arsi Diocese were selected for the study. The main purpose of the study was to analyze the scriptures from a religious point of view. The data was collected through observation, interview, and documentary data collection methods. Sanctification means: They are the various properties or resources of the church in which the various spiritual and divine services of God are performed. While the rules governing the EOTC are the same, sometimes the written rules and regulations apply differently. The fact that the church written law is unenforceable and shows that religious folklore implements the practice without changing the rule formally. If the EOTC can create a way for the sacraments to be completely self-sufficient according to the canon, or if it is established that they are orthodox traditions and canons before they are used, it may be a solution to the conflict.

[37] *ፍሬሕይወት ባዩ (ዶ/ር) (በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የፎክሎር ተመራማሪ)።*

# አኅፅሮተ ጽሑፍ

የዚኽ ጥናት ትኩረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ) የምትገለገልበትን ንዋያተ ቅድሳት ከሃይማኖታዊ ፎክሎር አንጻር ማሳየት ነው። ለጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ኹለት ከአርሲ ሀገረ ስብከት ኹለት አድባራት ተመርጠዋል። የጥናቱ ዋና ዓላማ ንዋያተ ቅድሳትን ከሃይማኖታዊ ፍክሎር እሳቤ አኳያ መተንተን ነው። መረጃዎቹ በምልከታ በቃለ መጠይቅ እና በሰነድ ምርመራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙ ናቸው። ንዋያተ ቅድሳት ማለት፤ የተለያዩ መንፈሳዊና መለኮታዊ የኾነው የእግዚአብሔር ቅዱስ አገልግሎትና ሥርዓት አምልኮ የሚፈጸምባቸው የተለዩ የቤተ-ክርስቲያን ንብረቶች ወይም ሀብቶች ናቸው፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የምትተዳደርበት ሕግ አንድ ኾኖ ሳለ የተጻፈው ደንብ እና የሚተገበረው የተለያየ መኾን ይስተዋላል። የተጻፈው ሕግ ሳይሻር በተግባር የሚታየው ከሕጉ ውጪ መኾኑ ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ያሳያል፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ በቀኖናው መሠረት ንዋያተ ቅድሳቱን ሙሉ በሙሉ ራሷን ችላ መሠራት የምትችልበትን መንገድ ብትፈጥር ወይም የተሠሩት ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትንና ቀኖናቸውን የጠበቁ ስለመኾናቸው ብታረጋግጥ ለተቃርኖው መፍትሔ ሊኾን ይችላል።

# 1. መግቢያ

ጥናቱ የኢ.ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ)ንዋያተ ቅድሳት በሚል መጠሪያ የሰየመችውንና ደንብ አውጥታ የምትገለገልባቸውን ቁሶች የሚመለከት ነው። ይኸ ጥናት በይበልጥ ትኩረት አድርጎ የሚመለከተው፤ ንዋያተ ቅድሳቱ ሃይማኖታዊ ደንብና መመሪያቸው በተግባር የተሻረ መኾናቸው ላይ ነው። ንዋያተ ቅድሳት ሲሠሩና አገልግሎት ላይ ሲውሉ ሃይማኖታዊ ደንብና መመሪያን ሽረው መመልከት በፎክሎር የጥናት መስክ ሃይማኖታዊ ፎክሎር በሚባል የጽንሰ ሐሳብ ትኩረት የሚጠና ነው።

ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ ይኸ ጥናት ከመደረጉ ቀደም ብሎ[38] የተለያዩ ግለሰቦች በተለያየ ምክንያት አጥንተዋል፤ ጽፈዋል። ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ ለዚኸ ጥናት የዳሰሳ ንባብ ሲደረግ ከተገኙት መካከል ቀዳሚው ሥራ ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ በ1963 ዓ.ም የተጠናው ነው[39]። ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ንዋያተ ቅድሳቱን በስም በመጥቀስ አገልግሎታቸውን እና ቅርጻቸውን በሥዕል አስደግፎ በገለጻ ማቅረብ ላይ ነው። ኹለተኛው በ1996 ዓ.ም "ኖኅተ ሰማይ" በሚል ርእስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው[40]። የዚኸ መጽሐፍ ትኩረት ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን በተመለከተ የእያንዳንዱን ንዋያተ ቅድሳት ምንነት፣ ተግባር፣ ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ፎቷቸውን ጭምር በዝርዝር ያስረዳል። ኹለቱም ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና ንዋያተ ቅድሳት የሚለውን ርእሰ ጉዳይ ይዘው መነሣታቸው ነው። ልዩነቱ ኹለቱም በሃይማኖታዊ ይዘቱ ላይ ብቻ ያተኩራሉ። የዚኸ ጥናት ትኩረት ደግሞ ኹሉንም ንዋያተ ቅድሳት መዘርዘር ሳይኾን ከሃይማኖታዊ ፎክሎር ጽንሰ ሐሳብ አኳያ ቁሶቹ ሲሠሩ፣ አገልግሎት ላይ ሲውሉ በማየት የሚገለገሉባቸውን በመጠየቅ ሃይማኖታዊ ደንቡን ያልተከተሉት ላይ ብቻ ያተኩራል።

---

38 ይኸ ጥናት ለዚኸ መጽሔት እንዲኾን ተጨማሪ መረጃ እና ሐሳብ ታክለበት እንጂ ቀደም ብሎ፤ "የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋየተ ቅድሳት ፎክሎራዊና ሃይማኖታዊ ገጽታ" በሚል ርእስ በ2000ዓ.ም (በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር" ለኹለተኛ ድግሪ ማሟያ) የተጠና ነው። እንዲኹም በኋላ ርእሰ ጉዳዩን በተለያየ መልኩ አስፍቶ በማጥናት መቐለ ዩንቨርሲቲ ያሬድ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥነ-ጽሑፍና ብራና ጥናቶች ማእከል ግንቦት 8/2009ዓ.ም በዚኸ ጽሑፍ አቅራቢ ለመድረክ ቀርቦ ነበረ።

39 ዐብይ ፍትሐአወቅ፣ "ንዋየ ቅድሳት" (ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1963ዓ.ም)።

40 ያሬድ ገ/መድህን፤ ኖኅተ ሰማይ፤ (ዐዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፤ 1996 ዓ.ም)።

የጥናቱ ዓላማ፤ የጥናቱ ዋና ዓላማ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋያተ ቅድሳትን ከሃይማኖታዊ ፎክሎር አንጻር ማሳየት ይኾናል። ዝርዝር ዓላማዎቹ፡-ሃይማኖታዊ ፎክሎር የሚታይባቸውን ንዋያተ ቅድሳት መለየት። እንዲኹም ንዋያተ ቅድሳትን ከሃይማኖታዊ ፎክሎር ትኩረት አኳያ መተንተን የሚሉ ናቸው።

የጥናቱ ጠቀሜታ፤ ለኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋያተ ቅድሳት ያሉበትን ኹኔታ ይጠቁማል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋያተ ቅድሳት በተመለከተ የቁሶቹን ቅርጽ፣ ማን መቼ እንዴት አገልግሎት ላይ ማዋልና መጠቀም እንደሚችል ምክንያቱን ጭምር በማብራራት ሃይማኖታዊ ደንብ ደንግጋላቸዋለች። ይኽንንም ደንብ በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት በተግባር እንዲውሉ ታዛለች። ኾኖም ቤተ ክርስቲያኗ ሰፊ አገልግሎት ከመስጠት እና ንዋያተ ቅድሳቱ ለረዥም ዘመናት አገልግሎት ሲሰጡ በመኖራቸው በተለያየ ምክንያት ለውጦች ይታዩበታል። እነዚኽን ለውጦች ርእሱ በፈቀደ መጠን በዚኽ ጥናት የሚታዩ ይኾናል። ስለዚኽ በንዋየ ቅድሳቱ ላይ የሚታዩት ለውጦች ምን እንደኾኑ ምክንያቱን በመለየት መፍትሔ ለመስጠት ይኽ ጥናት ጠቀሜታ አለው።

የጥናቱ ዘዴ፤ የንዋያተ ቅድሳቱን አሠራር አጠቃቀም፣ አያያዝና የት እንደሚገኙ ለመወሰን አሳሽና ገላጭ ዘዴዎች ተግባራዊ ኾነዋል። ለጥናቱ መረጃ የተሰባሰበው ከኹለት አህጉረ ስብከት ነው። አንዱ ከአርሲ ሀገረ ስብከት፤ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ሌሙ ማርያም ሲኾን። ኹለተኛው ደግሞ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም እና ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ነው።

የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የራሷ የኾነ ወጥ ዶግማ፣ ቀኖና፣ ሥርዓትና ትውፊት ያላት እነዚኽ ሃይማኖታዊ መመሪያዎቿ በማዕከላዊው ሲኖዶስ የሚዘጋጁና ለኹሉም አጥቢያ አብያተ-ክርስቲያን የሚደርሱ በመኾኑ አንዱን ቤተ-ክርስቲያን ብቻ በመመልከት ጥናቱን ማከናወን ይቻላል። ለዚኽ ጥናት አራቱ (ከከተማ እና ከገጠር ማቀላቀል ያስፈለገው) የጥናቱ ዓላማ ለኾነው ሃይማኖታዊ ፎክሎር ትንተና አስፈላጊ በመኾኑ ነው። ምክንያቱም ሃይማኖታዊ ፎክሎር ትኩረቱ ንዋያተ ቅድሳቱ በጽሑፍ የሰፈረ ሃይማኖታዊ ዝርዝር መመሪያ ምን ያኽል ተግባራዊ እንደኾነ ማየት በመኾኑ አራት አብያተ ክርስቲያን ተመርጠዋል። አራት አጥቢያ አብያተ-ክርስቲያን ከኹለት አህጉረ ስብከቶች ለመምረጥ፤ አብያተ-ክርስቲያኒቱን በቅርበት ማወቁና ተጠቃሚዎችን በቀላሉ ለማግኘት መፈለጉ የምቾት ናሙና ሲኾን ንዋየ ቅድሳቱ በተግባር ላይ ሲውሉ ለመመልከት የተለያዩ አህጉረ ስብከቶች ገጠርና ከተማ ማቀላቀሉ ደግሞ የዒላማ ናሙና ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ፤ ለጥናቱ አስፈላጊ ኾነው የተገኙት ከአራቱ አብያተ ክርስቲያን አንድ አንድ ካህን በአጠቃላይ አራት ካህናትና ኹለት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን በዓላማ ናሙና ለቃለ-መጠይቅ ተመርጠዋል፡፡ ለቃለ-መጠይቅ የተመረጡበት

ምክንያት የንዋያተ ቅድሳቱ ጠባቂዎችና ኀላፊዎች እነርሱ በመኾናቸው በህልውናቸውና በጠቀሜታቸው ላይ የተሻለ ዕውቀትና ልምድ ስለሚኖራቸው የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ። ኹለቱ ሊቃውንት ከንዋየ ቅድሳት ጋር ዝምድና ያላቸው ጽሑፎች በመጻፍና በማስተማር ጥልቅ የኾነ ዕውቀት አንዳላቸው በስሚ ስሚ (snow ball) ናሙና አወሳሰድ የተመረጡ ናቸው።

መረጃ ለማግኘት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና የሰነድ ምርመራ፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ምልከታ የተደረገባቸው በተመረጡት አብያተ ክርስቲያን፤ ንዋያተ ቅድሳት አገልግሎት ላይ ሲውሉ፣ እንዲኹም በዕቃቤቶች እና በሙዝየም የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳትን ናቸው። በምልከታ ወቅት ጥያቄ የፈጠሩ ሐሳቦችን ከካህናቱ እና ከሊቃውንቱ በመጠየቅ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። በሰነድ ምርመራ ወቅት በጽሑፍ ስለሰፈሩት ንዋያተ ቅድሳት ደንብ በተግባር ከሚታየውና ከሚተገበረው ጋር በተዛመደ ለጥናቱ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ከእያንዳንዱ መረጃ ሰጪ ጋር አጥኚዋ በአካል በመገኘት በመጠየቅ ምላሽ አግኝተዋል። በኹለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙት መረጃዎች የጥናቱ ዋነኛ አካል ኾነው በዚኽ ጥናት ውስጥ ቀርበዋል።

# 2. የጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፎች

## 2.1 ንዋያተ ቅድሳት

ንዋያተ የንዋይ ብዙ ቍጥር ነው፡፡ ንዋይ ገንዘብ ማለት ነው፡፡ ቅዱሳት ደግሞ ቅዱስ የሚለው ብዙ ቍጥር ነው፡፡ ቅዱስ ማለት ደግሞ የተለየ፣ የተከበረ፣ የተመረጠ ማለት ነው፡፡ ንዋያተ ቅድሳት ማለትም በቤተ-ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው የተቀደሱ ዕቃዎች ማለት ነው፡፡[41] ስለዚኽ ንዋይ ገንዘብ፣ ቅዱስ ደግሞ ልዩ የሚል ፍቺ በመያዝ ንዋያተ ቅድሳት ይኾናል። ንዋያተ ቅድሳት ሲባል ከመሰል ቁሶች ልዩ የኾነ በካህን የተባረከና ተለይቶ ለተቀደሰው አገልግሎት ብቻ የሚውል ማለት ነው። ኾኖም ቁሱን ልዩ ያደረገው ለአገልግሎት ከመዋሉ በፊት የሚደረገው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው። የሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ዋነኛ መሠረትም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት፣ ገበታውንም፣ [ዕ]ቃውንም ኹሉ መቅረዙንም፣ የዕጣን መሠውያውንም፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚኾነውን መሠውያና

[41]. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ መዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ (ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948ዓ.ም)፣ ገጽ 632።

[ዕ]ቃውንም ኹሉ የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ፡፡ ኹሉንም ትቀድሳቸዋለህ፣ ቅዱሳተ ቅዱሳንም ይኾናሉ፣ የሚነካቸውም ኹሉ ቅዱስ ይኾናል፡፡[42]

የብሉይ ኪዳንን መሠረት በማድረግ በሐዲስ ኪዳንም ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት ቅብዐ ቅዱስ[43] የተቀቡ ወይም በቅባት እና በቡራኬ የከበሩ ንዋያት ናቸው።

ወንጌላዊው ‹‹ደቀመዛሙርትማ መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ፡፡›› (የሐዋ. 11፥ 26) እንዳለው ቤተ-ክርስቲያን በአንጾኪያ ከተመሠረተች በኋላ የክርስትና እምነት ተከታዮች ቊጥራቸው ዕለት ተዕለት ይበዛ ነበር። የክርስትና እምነት ተከታይ ከኾኑት መካከል የተለያየ ሙያ ያላቸው ምእመናን ነበሩ። እነዚኽ ምእመናንም የቤተ-ክርስቲያን ምሥጢራት መገለጫ መገልገያ ዕቃዎችን ሠሩ፡፡ “የቤተ-ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ጻሕል፣ ጽንሐሕ፣ መስቀል እነርሱንም የመሳሰሉት ኹሉ ተሠሩ፡፡”[44]

ንዋያተ ቅድሳትን መሥራት ያለባቸው የተመረጡ የተሾሙና ጥበቡ ያደረባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን እንደነ ባስልኤልና ኤልያብ በእግዚአብሔር ተመርጠው “ጥበቤን በጥበበኞች ልብ አሳድራለሁ” ባለው መሠረት የተሾሙ ሰዎች መሥራት አለባቸው፡፡ በሚሠሩበት ጊዜ ምሳሌነታቸውንና የሚሰጡትን አገልግሎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ቅርጾችንና መልኮችን በማውጣትና በማስዋብ ይኾናል። የቤተ-ክርስቲያንን የአምልኮና ቀኖና ትውፊት ያልጠበቁ ዕቃዎች እንዲኹ ተሰብስበው ንዋያተ ቅድሳት አይኾኑም፡፡ ስለዚኽም ከመባረካቸው በፊት ይኽ ኹኔታ ይረጋገጣል፡፡ ትክክለኛ መኾናቸው ከታወቀ በኋላ ተባርከው ተገቢው ጸሎት ተደርሶላቸው ሜሮን ይቀባሉ፡፡ በሜሮንም ይከብራሉ፡፡[45]

አዲስ የተሠራ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ከኾነ ንዋያተ ቅድሳት በኹለት መልኩ ይባረካሉ፡፡ በተናጠልና በጋራ ጸሎታቸውም የተለያየ ነው ለምሳሌ ለጻሕል የሚደረግ ጸሎት፡-

> ኹሉን የሚይዝ እግዚአብሔር ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያኑን በንጽሕና ያጸናት ካህናቱንም ንዋያተ ቅድሳቱንም ቸር የምትኾን አብ ሆይ ከቸርነትህ እንለምንሃለን፡፡ ሰው ወዳጅ

---

[42]. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘጸ. 30፡26-30።

[43] ቅብዐ ቅዱስ - የተባረከ ቅባት በቤተክርስቲያን ለሥርዓተ ክርስትና መፈጸሚያ የሚያገለግል ከልዩ ልዩ ዕፅዋት ተቀምሞ የሚሠራ የሽቱ ዓይነት፡፡

[44] ሉሌ መልአኩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ (ዐዲስ አበባ፣ 1996ዓ.ም)፣ ገጽ 40።

[45] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘጸ. 40።

ሆይ ፊትህን ግለጽልን ባርከንም፡፡ ይኽችንም ያኽል ለሥርዓትና ለንጽሕና እንድትኾን ባርካት፡፡ የአንድ ልጅህን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን ያደርጉባት ዘንድ ይኽች ጻሕል የንጽሕና ጻሕል የበኰነትም ጻሕል ትኾን ዘንድ በርስዋም ላይ የአንድ ልጅህ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ይቀመጥ ዘንድ ከአንድ ልጅ ለሚገኝ ኃጢአት ስርየት አሜን።[46]

ከዚኽ በኋላ ካህኑ ሜሮኑን አንሥቶ ጻሕሉን በትእምርተ መስቀል በአራት ማዕዘን ውስጡንና ዙሪያውን ይባርከዋል፡፡ በዚኽ ዓይነት መልኩ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ለየራሳቸው የተዘጋጀው ጸሎት እየተጸለየላቸው በካህኑ እጅ በቅብዐ ቅዱስ በመስቀል አርአያ እየተባረኩና እየተቀቡ ይቀደሳሉ፡፡ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ንዋያተ ቅድሳት ይባላሉ፡፡ ከቤተ-መቅደሱ አገልግሎት ውጭ ሌላ ምንም ነገር አይደረግባቸውም፡፡ ስማቸውና ትርጉማቸውም ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር የተያያዘ ይኾናል፡፡ ኹሉም በአዲስነታቸው ከተባረኩ በኋላ በየጊዜው አገልግሎት ሲሰጡም እንዲሁ ካህኑ በንጽሕና መጠበቃቸውን እያረጋገጠ ይባርካቸዋል፡፡ ለኹሉም ንዋያተ ቅድሳት የሚጸለይና በተናጠል ለእያንዳንዱ የሚጸለይ ተብሎ ይከፈላል፡፡ ለአዲስ ንዋያተ ቅድሳትና አገልግሎት መስጠት ለጀመሩት ጸሎት ያስፈለገበትን ምክንያት ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> ንዋያተ ቅድሳት ከገበያ ተገዝቶ ሲመጣ የሚደረገው ጸሎት ሙሉ ለሙሉ ለውጥን የሚጠይቅ ጸሎት ነው፡፡ ምክንያቱም በረከሰ ወይም በቆሻሻ ቦታ የዋለ ያደረ የቆየ ዕቃ ስለኾነ ይኽንን ዕቃ ከርኩሰት ወደ ቅድስና ለመለወጥ የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ ይኽኛው ደግሞ ለጊዜው በዲያቆን እጅ ስለተነካ፣ በዲያቆናዊት እጅ ስለተነካ ያንን መጠነኛ ርኩሰት ለመለወጥ የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ ስለዚኽ ኹለቱ ጸሎታት ይለያያሉ፡፡[47]

ንዋያተ ቅድሳት ለተለየ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ስለኾነ ማንም ለግሉ ወይም ለቤት ውስጥ አገልግሎት እንዲፈጸምባቸው፣ አስመስሎም እንዲሠራ አይፈቀድለትም፡፡ ይኽን አድርጐም ቢገኝ ስሕተተኛና በደለኛ ይኾናል፡፡ የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የዘረፋቸውን ንዋያተ ቅድሳት በድፍረት ለመኳንንቶቹና ሚስቶች እንዲጠጡባቸው በማዘዙ እንደተዋረደና እንደተነቀፈ መንግሥቱም ከእርሱ እንደተወሰደች እንዲኹ መርገም ይኾንበታል[48]።

[46] ዳንኤል ሰይፈ ስላሴ፣ “ንዋየ ቅድሳትና የመስቀል 'የንዋያተ ቅድሳት' የቅዱሳን መጻሕፍት ሥርዓት”፣ (1994) ያልታተመ፣ ገጽ 4::
[47] Ibid
[48] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ት.ዳን. 5፣25-31።

የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት የሚተላለፍባቸው ቁሳዊ ሀብቶች ስለኾኑም በቤተ-ክርስቲያን ለእነርሱ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ በክብርና በንጽሕና ይቀመጣሉ አገልጋዮች "ወደ ውጭም ወደ አደባባይ በሚወጡበት ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፤ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩት…"።[49]

## 2.2 ፎክሎር

ፎክሎር "ፎክ እና ሎር" የሚሉ ኹለት ቃላት ቅንጅት ነው፡፡ "ፎክ አንድ የጋራ ነገር ያላቸው የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ይመለከታል።" ፤ "ሎር ደግሞ የጋራ የኾነውና የሚያገናኛቸው ጉዳይ ነው። ሰዎችን ከሚያገናኛቸው ጉዳይ ወይም "ሎር" አንዱ ትውፊት(tradition) ነው፡፡[50] ለምሳሌ በዚኽ ጥናት የፎክ ቡድን የሚባሉት የጋራ ጉዳያቸው ሃይማኖት ኾኖ የተሰባሰቡ ሰዎች ናቸው፡፡

ንዋያተ ቅድሳቱ ከቁስነታቸው ባሻገር በሚሰጡት አገልግሎት በሃይማኖት ዐይን መታየት ይገባቸዋል፡፡ ሃይማኖት በራሱ አንድ የጥናት መስክ ሲኾን ፎክሎር ደግሞ ከታሪክና ተጨባጭ ኹኔታዎች ጋር ተያይዞ የሚሰፋና የሚለጠጥ ልዩ የኾነ ኺደት ነው፡፡[51] በተለይ የሃይማኖትና ፎክሎርን ግንኙነቱንና ልዩነቱን በስፋት መመልከቱ ለዚኽ ጥናት ወሳኝ ጉዳይ ነው።

## 2.3 ሃይማኖታዊ ፎክሎር

"ሃይማኖታዊ ፎክሎር ሃይማኖታዊ ልማድንና ሃይማኖታዊ ያልኾነ ልማድን የሚመረምሩበት መነፅር ነው፡፡[52]" ሃይማኖታዊ ፎክሎር ሀገረ-ሰባዊ ልማድንና በሃይማኖት ሥርዓቶች መካከል ያለውን ቁርኝት ያሳያል። ትኩረቱ በታወቁት የሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ፣ ሰዎች በየራሳቸው (የሃይማኖቱ አማኝና ተከታይ መኾናቸው ሳይቋረጥ ማለት ነው) በሚከተሏቸው እምነቶችና በሚፈጽሟቸው እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ ከንዋያተ ቅድሳቱ መካከል ሃይማኖታዊ ግልጋሎቱ ሳይቀር፣ ሃይማኖታዊ ደንቡ ሳይለወጥ በተለያየ ምክንያት

---

[49] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ሕዝ.44፣18።

[50] Dundes, A.The study of Folklore, (Prentice-Hall, Inc, Engle wood, cliffs, N.J,1965), pp 2.

[51] Mathisen S. "Folklore" in Fekade Azeze, "Teaching Material selected and compiled riders for EtLi 621" of Ethiopian languages and literature, M.A. in Ethiopian literature and Folklore, 2003.

[52] Larry, D. "Religuse folklore", in Fekade Azeze, "Teaching Material selected and compiled, riders for EtLi 621" of Ethiopian languages and literature MA in Ethiopian literature and Folklore, 2003.

ከደንቡ ያፈነገጡ ንዋያተ ቅድሳትን ለመመልከት የሚያስችል የጽንሰ ሐሳብ መነሻ ነው።

ሃይማኖታዊ ፎክሎር በተለያዩ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ውስጥ ሊገኝ ይችላል። በታወቀው ሥርዓተ አምልኮ ወይም ከታወቀው ሥርዓተ አምልኮ ውጭ ዶክትሪኑ የሚያዘውን ሊያሟላ አንዳንዴ ሊቃረን፣ እንዲኹም ልዩ ልዩ የተዛመዱ ዘውጎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ተመሳሰሎውን ወይም ተቃርኖውን አልያም ዝምድናውን ለመለየት ሃይማኖታዊ ደንቡን እና ተግባራዊነቱን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ለመመርመር መነሻው ሃይማኖታዊ ይዘቱ መኾን አለበት።[53] የሃይማኖታዊ ፎክሎር ጽንሰ ሐሳብን በመያዝ በዚኽ ማዕቀፍ ውስጥ ሊታዩ የሚችሉትን ንዋያተ ቅድሳት ብቻ ይዳሰሳሉ። ንዋያተ ቅድሳቱ ያላቸውን ሃይማኖታዊ ይዘት በቅድሚያ በመግለጽ፣ ፎክሎራዊ መልኮቹን ደግሞ በማስከተል የሚተነተን ይኾናል።

# 3. የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ፎክሎር

ንዋያተ ቅድሳት የምንላቸው በጥቅሉ ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ጀምሮ መገልገያ ቁሶቹን በሙሉ ነው። የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የምትገለገልበት ንዋያተ ቅድሳት የአሠራሩን መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በተግባር የሚሠሩት የሃይማኖቱ ተከታዮች ወይም ጥበቡ ያላቸው ግለሰቦች ሲኾኑ ለንዋያተ ቅድሳቱ መሥሪያ የሚውለው ጥሬ ዕቃ በአብዛኛው በሀገራችን የሚገኝ ነው።[54]

የንዋያተ ቅድሳት አጠቃላይ ዝርዝሮቹን ስንመለከት፡- ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን እና በሮቹ፣ ጉልላት፣ ሻኩራዎች፣ በአጸድ ውስጥ የሚገኙ ቤተ-ልሔም፣ ግብር-ቤት፣ ክርስትና-ቤት፣ ደወልና ሌሎችም ይገኙበታል። በሕንጻ ቤተ-ክርስቲያኑ ሦስት ክፍል (ቅድስት[55]፣ መቅደስ[56]እና ቅኔ ማሕሌት[57]) ከነመገልገያ ቁሶቹ ንዋያተ ቅድሳት ናቸው። ከእነዚኽህም፤ በቅኔ ማሕሌት፡- ለመዝሙር አገልግሎት የሚውሉ ንዋየ ቅድሳት ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋምያ፣ ሥዕላት፣ መጻሕፍት፣ አትሮንስ፣ መቅረዝ እና መጋረጃ ናቸው።

[53]Ibid.

[54] ፍሬሕይወት ባዩ። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ"ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለ ኤም ኤ. ዲግሪ ማሟያ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር፤(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 2000)፣ ገጽ 63።

[55] ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉ ምእመናን፣ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት የሚፈጽሙ ሙሽሮችና ከቀዳስያን ውጪ ያሉ ካህናት ተሰጥኦ በመቀበል ቆመው የሚያስቀድሱበት ክፍል ሲኾን ማንኛውም ምእመን እዚኽ መቆም አይችልም።

[56] በብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን በመባል የሚታወቅ ሲኾን ሦስት በሮች አሉት፡፡ በሦስቱም በሮች ላይ መጋረጃ እኩል ይጋረዳል፡፡ መሥዋዕት የሚቀርብበት ታቦተ ሕጉ የሚቀመጠው በዚኽ ክፍል ሲኾን ከካህናት በስተቀር ማንም አይገባም፡፡ ካህናትም የሚገቡት ለአገልግሎት ብቻ ነው(የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን፣ 1994፡26)፡፡

[57]ወደ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥ ክፍሎች ስንገባ የመጀመሪያው ክፍል ቅኔ ማሕሌት ይባላል፡፡

በመቅደስ አገልግሎት የሚሰጡ ንዋየ ቅድሳት በርካታ ናቸው። እነዚኽም፡-ታቦት፣ ልብሰ ተክህኖ፤ ዘውድ፣ መንበር፣ ጽዋዕ፣ ዕርፈ-መስቀል፣ ጻሕል፣ ዐውድ፣ አጎበር፣ መነሳነስ(ጭራ)፣ መሶበ ወርቅ፣ ብርት፣ ሰን፣ ጽንሐሕ፣ ሙዳይ፣ መጎናጸፊያ፣ ቀጸላ፣ ቃጭል፣ መስቀል(የመጾር መስቀል)፣ ማኅፈድ፣ ጥላና ሌሎችም ይገኙበታል። ጥላ፣ ቃጭልና ሌሎችም በቅኔ ማሕሌትና በመቅደስ እየተዘዋወሩ አገልግሎት የሚሰጡ ሲኾኑ በተለያዩ ዓመታዊ ክብረ በዓላት ላይ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ንዋያተ ቅድሳትም አሉ።

## 3.1 የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ

ከንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ነው። የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ የተለያየ ነው፡፡ "በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሦስት ዓይነት የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር አሉ፡፡ እነዚኽም ሰቀላማ፣ ክብ(ቤተ-ንጉሥ) እና ፍልፍል፡፡"[58] በዚኽ መሠረት የአራቱን ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ ስናይ ሶስቱ ክብ ሲኾኑ የውስጥ ክፍላቸው ቅድስት መቅደስና ቅኔ ማሕሌት አላቸው። ለሐዲስ ኪዳን ቤተ-ክርስቲያን መሠረቱ ብሉይ ኪዳን ነውና ሦስት ክፍል መኾኑና ክብ መኾኑ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ምሳሌ ነው፡፡ የሐዲስ ኪዳን ቤተ-ክርስቲያን በፊልጵስዩስ የተሠራችው ክብ ነበረች፡፡ ክብ መኾኗም የፍጹምነት ምሳሌ ነው፡፡

"ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ሲታነጽ ምሥጢር እንዳይፋለስ፣ አሠራሩ ትርጉም አልባ እንዳይኾን አበው ይጠነቀቁበታል፣ ቅርጹ ከክርስቶስ የዓለም ቤዛነት ጉዞ፣ ከቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ተጋድሎ ጋር እንዲያያዝ ኾኖ ነው፡፡[59]" የሦስቱን ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ክብ የመኾንና በውስጥ ክፍሎቻቸው ክፍፍል እንዲኾም ከውጭ ያሉትን ጉልላት እና ሻኩራ ምሳሌነት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ክብ አይደለም፤ የውስጥ ክፍሎቹ ኹለት ሲኾኑ ጉልላትና ሻኩራም የለውም። ክብ ላለመኾኑ እና ኹለት ክፍል ለመኾኑ ምክንያት የኾነው የቀድሞዎቹ ሕንጻ አብያተ-ክርስቲያን አርጅተው በምትካቸው አዲስ ሲሠራ ክብ የነበረ ቅርጻቸው ይቀየራል። የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንም በዚኹ ምክንያት ቅርጹ ተቀይሯል። የቀድሞ ክብ እና ባለሦስት ክፍል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለምን እንደተቀየረ የአዲሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሲጣል የነበሩት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሲገልጹ፡_ "ዘመናዊ የኾነው የቤተ

---

[58] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን፣ ትላንትና ዛሬና ነገ፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተር ኘራይዝ፣ 1994 ዓ.ም)፣ ገጽ፣ 27፡28።
[59] ያሬድ ገ/መድህን፣ ኖኅተ ሰማይ፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርኘራይዝ፣ 1996ዓ.ም)፣ ገጽ 47።

ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ ይኸ ስለኾነ መርጠነዋል፤[60]" በማለት መልሰዋል። የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ክብ የኾነውን የቅርጽ ለውጥ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲገልጹ "ቤተ-ክርስቲያን ምኩራብ እንጂ ቤተ-ክርስቲያን አይመስልም፤ ስሙን ግን ካቴድራል ይሉታል።[61]" በማለት ይመልሳሉ።

**ጉልላት፤** በቤተ-ክርስቲያን አናት ላይ የሚቀመጥ ክብ ኾኖ በንጉሥ ዘውድ ወይም በቁም መሶብ ቅርጽ የሚሠራ፤ በአናቱ ላይ መስቀል ያለው፤ በመስቀሉ ዙሪያ የእንቁላል ቅርጽ ያላቸው ብረት ነክ ማዕድናት በዚያም ላይ የሰጐን እንቁላል የተሰካበት ነው፡፡ በመስቀሉ ላይ መሰካት ያለበት የሰጐን እንቁላል እንደኾነና ቁጥሩም ሦስት አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ወይም ዐሥራ ኹለት መኾን አለበት፡፡[62] እንጦጦ ማርያም የሰጎን እንቁላል ለምን በጉልላቱ ላይ አልኖረውም ለሚለው ምላሽ ሲሰጡ፡_"አኹን የሰጐን እንቁላል ከየት ይገኛል? የሰጐን እንቁላል መኾኑ ግን ብዙ ሐተታ ነበረው።[63]" በማለት የሰጎን እንቁላል አለመገኘቱን በምክንያትነት ጠቅሰዋል።

**ሻኩራ(መርገፍ)፤** ከብረት ነክ ማዕድናት ይሠራል። በክብ ቅርጽ በሚሠራ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ጣሪያ ላይ ክፈፉን ይዞ ዙሪያውን የሚንጠለጠሉ ናቸው። ሻኩራ ነፋስ ሲነፍስ በመንቀሳቀስ እርስ በእርስ ሲነካኩ ድምጽ ይሰጣሉ፡፡ ድምጹ እና እንቅስቃሴያቸው ሃይማኖታዊ ተምሳሌትነቱ፡-"ቅዱሳን መላእክት ሌሊትና ቀን በቤተ-ክርስቲያን አጸድ ያሸበሽባሉ ይዘምራሉም።[64]" የሚለውን ማሳያ ነው። በእንጦጦ ማርያም እና ሌሙ ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሻኩራ ያላቸው ሲኾን ኹለቱ ግን የላቸውም።

በአጠቃላይ የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ ሲለወጥ ሙሉ በሙሉ ከቀሩ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ጉልላት እና በጉልላቱ ላይ ያለው የሰጎን እንቁላል (የሰጎን እንቁላል ቅርጽ) እንዲኹም ሻኩራ ናቸው። ክብ የኾነው እና ጉልላት የነበረው የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ ሲቀር ቀድሞ የነበረው የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቀኖና ተምሳሌታዊ ፍቺ አዲስ በተተኩት የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ አልተሻሻሉም።

## 3.2 ልብሰ ተክህኖ

ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ከሚያሳዩ ንዋየ ቅድሳት ልብሰ ተክህኖ ይገኝበታል። ልብሰ ተክህኖ በቅዳሴ ጊዜ ቀዳስያን የሚለብሱት ልብስ ነው፡፡ የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች

---

60 መረጃ ሰጭ፡- በኩረ ትጉሀን ቀሲስ በለጠ ኃይለማርያም፣ እድሜ 32፣ (ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 17 2000)፡፡

61 መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 15 2000)፡፡

62 ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፤ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ (ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992ዓ.ም)፣ ገጽ 12።

63 መረጃ ሰጭ፡- መምህር ቃለ ጽድቅ፣ እድሜ 71፣ (ቃለ-መጠይቅ ሚያዝያ 6 2000)፡፡

64 ያሬድ ገ/መድህን፣ ኖኅተ ሰማይ፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 1996ዓ.ም)፣ ገጽ 60።

በአገልግሎት ወቅት የሚለብሷቸው ልብሰ ተክህኖ የመልበሻ ጊዜ፣ የልብሱ ዓይነት፣ አዘገጃጀቱ (አሰፋፉ)፣ መጠኑ፣ ቀለማቸውና ሌሎችም የየራሳቸው ደንብ እና ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ያላቸው ናቸው።

ካህናት መሥዋዕት ለማቅረብ ሲዘጋጁ፣ ልብሰ ተክህኖውን በኤጲስ ቆጶስ አስባርከው ኤጲስ ቆጶስ ከሌለ ራሳቸው ባርከው ይለብሳሉ፡፡ ካህናት የሚለብሱት የስረኛው ቀሚስ፣ የላይኛው ካባ ላንቃ ነው፡፡ ካባ አምስት መንዲል ያለው ሲኾን ኹለቱ በፊት ለፊት ሦስቱ ከጀርባ ይወርዳል፡፡ አምስት መሆኑ የካህኑ እምነት በአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ላይ የተመሠረተ መኾኑን ያመለክታል፡፡ ከአናታቸው ላይ የሚደፉት አክሊል ይባላል፡፡ ጌጥ ያለው ክብ ሆኖ አናቱ ላይ መስቀል፣ ከውስጥ ከቀላልና ጠንካራ ቁስ ይሠራል[65]፡፡ ምሳሌነቱ 'የክርስቲያን ፍጻሜው የድል አክሊል ነው' የሚል ነው።

የዲያቆናት ልብስና አክሊል ከካህኑ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ካህኑም ኾነ ዲያቆኑ ልብሰ ተክህኖ ሳይለብሱ መቀደስ አይችሉም፡፡ ጳጳሳት ግን በልብሳቸው መቀደስ ይችላሉ፡፡ ክህነት ያላቸው መነኮሳት ሞጣህት ብቻ ደርበው በራሳቸው ቀሚስ መቀደስ ይችላሉ፡፡ የጳጳሳትና የመነኮሳት አክሊል ሳይኾን አስኬማ ይበላል፡፡ አስኬማ ጌታ ሲሰቀል አይሁድ በስቅለቱ ጊዜ እሾህ ጕንጉነው በራሱ ላይ የመድፋታቸው ምሳሌ ነው። የጳጳሳትም ልብስ እጁ ሠፊ ሲኾን ስፋቱ ብዙ መክሊት እንደተሰጣቸው ለማመላከት ነው፡፡

ተክህኖ ልብስን በተመለከተ ከቀኖናው የወጣ ስለመኾኑ ለዚኽ ጥናት ምልከታ ሲደረግ በተደጋጋሚ የታየው ቀለማቸው ከተጻፈው ደንብ ጋር አለመመሳሰል ዋነኛው ነው። የካህናት አለባበስን በተመለከተ ሃይማኖታዊ ደንቡ "ካህናት የሚቀድሱባቸው አልባሳት ቀይ ቀለም የገባባቸው ያይደለ፣ ነጫጭ ይኹኑ። ነጭ ልብስ ደስ እንዲያሰኝ በሥጋ ወደሙ የተገኘ ክብርም ደስ ያሰኛልና።[66]" በማለት ይገልጻል።

በአራቱም አብያተ ክርስቲያናት ያሉ የመቀደሻ ልብሶች ለምልከታ ከተሔደባቸው አራት አራት ቀናት ሌሙ ማርያም ከአራቱ ቀን በአንዱ ነጭ ለብሰው ቀድሰዋል፡፡ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ አንድ ቀን በጥቍር (የጸሎተ ሐሙስ ዕለት)፣ አንድ ቀን ነጭ (የትንሣኤ ዕለት) እንጦጦ ማርያም አንድ ቀን (የሆሣዕና ዕለት) ነጭ ሲለብሱ፣ በሌላው ቀን ግን የተለያየ ቀለም ያላቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሲቀድሱ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የካህናት ልብሰ ተክህኖ ቀለም ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ነጭ አለ። ከላይ በፍትሐ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ እንደተገለጠው ሕጉ እና ትውፊት ነጭ እንዲለብስ ቢያዝም በተግባር ግን ተዘውትሮ ሲከወን እንመለከታለን።

---

[65] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፥ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘሌ.8፥9፤ ማር.15፥1።

[66] ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ፣ አሥመራ፣ (ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1956፡)፣ አን.12፥196

ነጭ ቀለም ያለው ልብሰ ተክህኖ ለምን እንደማይለብሱ አገልጋዮች እንደ ምክንያት የሚያነሡት ልብሱን የሚሸጡ ነጋዴዎች ነጭ በብዛት አለማቅረባቸውን ነው። በገበያ ላይ እንደልብ ላለመገኘቱ ምክንያቱ ሲጠቁሙ በካህናቱ ልብስ ላይ የተለያዩ ጌጣ ጌጦች ይሰራሉ። ነጭ ላይ ደግሞ ጌጣጌጡ አያምርም ወይም ለገዢው ሰው አይን(ቀልብ) አይስብም፡፡ በልብሰ ተክህኖ ላይ የሚደረገው ጌጥ ከቀኖናው ውጭ ነው፡፡ ሌላው ሊቃውንቱ የተክህኖ ልብሶች ቀለም በቀኖናው መሠረት ነጭ ላለመኾኑ ከሚያነሧቸው ምክንያቶች "ከእኅት አብያተ-ክርስቲያን የተወረሰ ልምድ ሊኾን ይችላል[67]" የሚል ግምት ነው፡፡

የተክህኖ ልብስ ኹለተኛው ሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያ ቀሚሱ እስከ ተረከዝ የረዘመ መኾን እንጂ አጭርም ከመጠን ያለፈ ረዥምም መኾን እንደሌለበት ሲገልጽ፣ "ካህናት በቅዳሴ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ እስከ ተረከዛቸው የሚደርስ ይኹን … ልብሱ ተርፎ አካሉ ቢያጥር በመለኮት ሕፀፅ አለበት፤ ሥጋ ምልዓት ኾኖታል ያሰኛል፡፡[68]" በማለት ሃይማኖታዊ ደንቡ ተጽፎ ይገኛል። ስለዚኽ ቀዳስያን የሚኾናቸውን ልብሰ ተክህኖ አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት መርጠው መልበስ አለባቸው፡፡ ለረዘመ ቀሚስ መታጠቂያ (ዝናር) እንዲታጠቁ ምሳሌው ጭምር አለ፡፡ ቀሚስ የመለኮት ምሳሌ ነው፡፡ ቀሚሱን የሚለብሰው ካህኑ የሥጋ ምሳሌ ነው፡፡ መታጠቂያው ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ሲኼድ አይሁድ ወገቡን በገመድ አስረው የማንገላታታቸው ምሳሌ ነው፡፡

በምልከታ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስና በእንጦጦ ማርያም የለበሷቸው ልብሰ ተክህኖ አጫጭር ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ የልዑካን ልብስ ቀለሙ፣ አሰፋፉ፣ እንዲኹም መጠኑ ከቀኖና ውጭ እንዳይኾን አገልጋዮች በየ ጊዜው ስለ አልባሳት ቀለም ትርጉምና ትውፊቱን መጠበቁ ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ ትኩረት የሚያሻው መኾኑን አጥኝዋ በምልከታው ተገንዝባለች፡፡

---

[67] ለምሳሌ የግሪክን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የቅዳሴ ልብሶች ቀለም፤ በነቢያት በዓል የሚቀድሱት አረንጓዴ ለብሰው ሲሆን ምሳሌነቱ የነቢያት ስብከት "ጌታ ይወለዳል፣ ዓለምን ያድናል" የሚል ተስፋ የነበረው ነው፡፡ አረንጓዴ የቅጠሎች ቀለም በመሆኑ ፍሬ የማፍራትን ተስፋ የሚያሳይ ቀለም ያለው ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ በሐዋርያትና በሰማዕታት በዓል ቀይ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ ቀይ ሰማዕታትና ሐዋርያት በዚህች ምድር ሲኖሩ ስለ ክርስቶስ የሰበኩት በቃል ብቻ ሳይሆን መከራዎችን እየተቀበሉ፣ ደማቸውን እያፈሰሱ ስለነበረ ቀይ ቀለም የደማቸው ምሳሌ ሆኖ ተመርጧል፡፡ የጻድቃንና የጌታ በዓል ከሆነ ደግሞ ነጭ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ የነጭ ምሳሌ ጌታ ከሙታን ተለይቶ በተነሳ እለት መቃብሩ አጠገብ ነጫጫ የለበሱ መላእክት ታይተዋል። እንዲሁም ጌታ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ገልጧል። ብርሃን ደግሞ እንደ ነጭ ቀለም የሚታይ ስለሆነ በጌታና በጻድቃን በዓላት ነጭ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ በአጠቃላይ ቀዳስያን በኢ.ኦ.ተ.ቤ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ልብሶች ለብሰው የሚቀድሱበት ምክንያት ከእህት አብያተ ክርስቲያናት በመጣ ልማድ ሊሆን ይችላል( ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ ቃለመጠይቅ)፡፡

[68] ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ፣ አሥመራ፣ (ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1956፣)፣ አን.12፣196።

## 3.3. ድባብ/ጥላ

ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ከሚያሳዩ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ጥላ ይገኝበታል። ድባብ(ጥላ)፤ ድባብ የሚባለው ትልቅ ጥላ ነው። ድባብ ለክብረ በዓል ታቦት ሲወጣ (ሲነግሥ) አገልግሎት ላይ የሚውል ነው፡፡ ድባብም ኾነ ጥላ ዘንጉ፣ ከብረት ነክ ማዕድናት እንዲኹም ከእንጨት ይሠራል። ከላይ ያለው ጨርቅ ሲኾን ጨርቅነቱ የተለያየ ሊኾን ይችላል፡፡ ጥላ አገልግሎቱ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ ኅብስቱን ከቤተ-ልሔም ወደ ቤተ-መቅደስ ይዞ ሲኼድ፣ ካህኑ ማዕጠንት ይዞ ከመቅደስ ወደ ቅድስት ለማጠን ሲወጣ በዲያቆኑ የሚያዝ ነው፡፡ ወንጌል ሲነበብ ሥጋ ወደሙ ለምእመናን ሲሰጥ (በዕርገት ጊዜ) ከቅዳሴም ውጭ አስከሬን ወደ መቃብር ሲወርድ ይዘረጋል፡፡ ምሳሌነቱ ሕዝበ እስራኤል አርባ ዓመት ሙሉ ሲጓዙ የፀሐዩ ግለት እንዳያቃጥላቸው የእግዚአብሔር መልአክ በደመና ይጋርዳቸው ነበር፡፡ ዛሬም ክርስቲያኖች ወደ መንግሥተ ሰማያት በሚያደርጉት ጉዞ የእግዚአብሔር ጥበቃ (ከለላ) እንደማይለያቸው ማሳያ፤ እንዲኹም ሙሴ ጽላቱን ሲቀበል በደብረ ሲና ተራራ የጋረደው ደመና ምሳሌ ነው፡፡ በደብተራ ኦሪት ታቦት ሲወጣ እግዚአብሔር ለነሙሴ ሲገለጥላቸው ድንኳኗ በደመና ተሞልታ በደመናው መካከል ክብና ልዩ ብርሃን መጥታ በታቦቱ ላይ ትረብ ነበር፡፡ ድባቡም የዚኽ ብርሃን ምሳሌ ነው፡፡ ያኔ በደብተራ ኦሪት በታቦቱ ላይ ይገለጥ የነበረው ብርሃን ዛሬም እንዳልተለየ ለማጠየቅ ነው[69]፡፡

በአራቱም አብያተ ክርስቲያናት በተለያየ ቀን በተደረገ ምልከታ በድባብና በተለያዩ ጥላዎች ላይ ሥዕለ ቅዱሳን ተሥሎባቸው ይታያል። በጥላ ወይም በድባብ ላይ ሥዕል እንዲሳልበት አልተፈቀደም። አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ጥላዎች ላይ ግን በብዛት ቅዱሳት ሥዕላት ተለጥፎባቸዋል። ኾኖም በቀኖናው ሥዕለ ቅዱሳን በጥላ ላይ እንዲሳሉ አልታዘዘም፡፡ ምክንያቱም ሥዕለ ቅዱሳን በራሳቸው ንዋየ ቅድሳት ሲኾኑ ሊሰጣቸው የሚገባ አክብሮት በጥላው የላይኛው ክፍል ላይ እንዳይኾኑ ምክንያት ይኾናል።

## 3.4 ተቋመ ማኅቶት (መቅረዝ)

የተቋመ ማኅቶት አሠራር ቅርጽ የሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያ ነው። ተቋመ ማኅቶት፣ ተቋመ ወርቅም ይባላል፡፡ ተቋም፣ መቅረዙን መሸከሚያ ማለት ሲኾን፣ ማኅቶት መብራት ነው፡፡

[69] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ መጽሀፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ 1ኛ ነገ. 6፣2 ፤ ዘዳ.19፣9፤ 9፣3።



ስእል 1 ማኀቶት

የሚበራው ቀንዲል ወይም ሻማ ሊኾን ይችላል፡፡ በብሉይ ኪዳን ሙሴ እንዲሠራቸው ከታዘዛቸው ሦስት ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ነው[70]። ተቋመ ወርቅ የተባለው የሚበራው በዘይት ስለነበረ አሠራሩም ከወደታች ቀጥ ብሎ እንዲቆም እንደ ጽዋዕ ያለ እግር ይሠራለታል፡፡ መካከለኛውን አንድ ወጥ  አድርጎ እንዲያበጅና ሦስቱን የመቅረዙን ቅርንጫፎች ከግራና ከቀኝ በማድረግ በመካከለኛው ላይ የተሞላውን ዘይት በስድስቱም እንዲሞላ መኮስተሪያ እንዲያበጅለት አዟል፡፡ ምሳሌነቱ ተቋሙ የድንግል ማርያም፣ ፈትሉ አምላክ የነሣው ሥጋ፣ ዘይቱ የመንፈስ ቅዱስ እሳቱ የመለኮት ቅርንጫፎቹ ሰባት መኾናቸው የፍጹምነት ምሳሌ ነው፡፡ ሰባት በዕብራውያን ፍጹም ነው[71]፡፡ በቀኝና በግራ ሦስት ሦስት መኾናቸው በዘመነ መሳፍንት፣ በዘመነ ነገሥት፣ በዘመነ ካህናት የተጻፉ መጻሕፍት ምሳሌ ነው፡፡ የተቋመ ማኀቶት ቅርጽ ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት የሚከተለውን ይመስላል።

ከላይ ፎቶ ላይ የምንመለከተው በቆጂ ደብረ ፀሐይ  ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተነሣ ፎቶ ሲኾን ቀኖናውን ተከትሎ የተሠራ ነው። ቀኖናውን ካልጠበቁ ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ተቋመ ማኀቶት ነው፡፡ ቀኖናውን ያላሟሉ ሌሎች ተቋመ ማኀቶት በዚኹ ቤተ ክርቲያን የሚገኙ ሲኾን ማብሪያቸው ባለ አምስት፣ ባለሦስት እና ባለኹለት ናቸው። እንዲኹም ሌሙ ማርያም ባለ ሦስት እንጦጦ ማርያም ባለ አንድ ማብሪያ ተቋመ ማኀቶት ይገኛሉ፡፡

70 የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፀ.25፣31-40፣ 37፣24፣ ዘዳ. 9፣4።

71 የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፣ መጽሀፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣  ምሳ. 24፣ 16 ።

# 3.5 ከበሮ

በሚሰጡት አገልግሎት ሃይማኖታዊ ፎክሎር ከሚታይባቸው ንዋያተ ቅድሳት ከበሮ ይገኝበታል። ከበሮ ለማሕሌት አገልግሎት ከሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ነው። ከበሮ ቋሚው አካል ከዕንጨት ወይም ከከበሩ ብረት ነክ ማዕድናት ለምሳሌ ከብር ወይም ከወርቅ ተሠርቶ ከላይና ከታች እንዲኾም የሚጠላለፈው መወጠሪያና ማንገቻው በከብት ቆዳ የሚሠራ የዜማ መሣሪያ ነው፡፡ ቅርጹ ከአንድ ወገን ሰፊ፣ ከአንድ ወገን ጠባብ ሲኾን ሲመታ በመቺው አንገት ላይ በማንጠልጠል ሰፊው እና ከፍ ያለ ድምጽ የሚያሰማው ክፍል በቀኝ እጅ ጠባቡ በግራ እጅ ይመታል፡፡ የመዝሙር መሣሪያ ስለመኾኑም "ስሙን በማሕሌት ያመስግኑ፣ በከበሮና በመስንቆም ይዘምሩለት[72]" በማለት ስለአገልግሎቱ ተገልጿል፡፡ ታቦተ ጽዮንን ከአሚናዳብ ቤት ባወጡ ጊዜ ዳዊትና የእስራኤል ቤት ኹሉ በቅኔና በበገና በመስንቆና በከበሮ በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት…ይዘምሩ ነበር፡፡[73] በተጨማሪም ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን ከበሮ እየመታችሁ አመስግኑ፡፡[74]

የከበሮ ምሳሌነቱ፤ ከላይና ከታች ተጠላልፎ እንደመወጠሪያ የሚያገለግለው ጠፊር(ቆዳ) አይሁድ ጌታን በገረፉት ወቅት ሰውነቱ ላይ የወጣዉን ሰንበር ያስታውሳል። በአንገት መነገቱ በአንገቱ ገመድ አስገብተው ያንገላቱት፣ ከላይ ሰፊ መኾኑ ኹሉ ነገር ያለውን እግዚአብሔርን ሲያመለክት ከታች መጥበቡ ወልድ በጠባብ ደረት የመወሰኑ ምሳሌ ነው፡፡ በዚኹ መሠረት በአራቱም አብያተ ክርስቲያን በእያንዳንዱ ከኹለት በላይ ከበሮ ይገኛል።

በምልከታ በተገኘው መረጃ በንግሥ በዓል(በዓመታዊ ክብረ-በዓል) በተለይ በሌሙ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ካሉት ከበሮዎች አንዱ ለዘፈን ሲገለገሉበት ነበር። በተጨማሪም ከቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ ጋብቻ ለሚፈጽሙ ምእመናን ለሰርግ ዘፈን ማጀቢያ ከበሮ በውሰት ከቤተ-ክርስተያን ለምእመናን ይሰጣል። በከበሮ ላይ የሚታየው ሃይማኖታዊ ፎክሎር አጠቃቀም ላይ ነው። ይኸውም ለአምልኮ ተግባር ለምስጋና የሚያገለግልን ንዋየ ቅድሳት ለዓለማዊ ተግባር ወይም ለዘፈን መዋሉ ነው።

72. የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ መዝ.148፣3።

73 የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ 2ኛ ሳሙ.6፣5።

74 የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዮዲት፣ 16፣ 2።

# 3.6 ሥዕል

*ሥዕል፤* "በቁም መልክ፣ የመልክ ጥላ፣ ንድፍ፣ አምሳል፣ ንድፍ በውኃ፣ በመጽሔት፣ በጥልፍ፣ በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ ተጽፎ ከደብር፣ ከዕብን፣ ከዕፅ፣ ከማዕድን ታንጦ፣ ተቀርጦ፣ ተሸልሞ፣ አጊጦ የሚታይ የሚዳሰስ ነገር ነው፡፡[75]››

ሥዕለ ቅዱሳን በሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን የሚሳሉበት ደንብ አላቸው። በብሉይ ኪዳንም በታቦተ ሕጉ ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥል ሙሴ ታዞ ነበር፡፡[76] እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቅዱሳት ሥዕላት ለሥርዓት አምልኮ መፈጸሚያ ይውላሉ፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ትእዛዝ አብነት አድርጎ ጠቢቡ ሰሎሞን ታላቁን ቤተ መቅደስ ካሠራ በኋላ ሥዕለ ኪሩቤልን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አስቀምጧል፡፡ በቤተ መቅደስ ግንብ ዙሪያ በበሮች ላይ የኪሩቤልንና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳ አበባ ሥዕሎችን ሠርቷል።[77] ሥዕለ ቅዱሳንን ከክርስትና ሃይማኖት በፊት አይሁዶች ለአምልኮ ሥርዓት ይገለገሉባቸው ነበር፡፡

በቤተ-ክርስቲያን ሥዕል ለመሣል ምክንያት የነበረው የክርስትናን ሃይማኖት ለማስተማር በቂ መጻሕፍት ስላልነበሩ እና እንደልብ ለማስተማር ስለማይፈቀድ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በሥዕል እያቀረቡ በቀላሉ ለማስተማር ይገለገሉበት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ይሣሉ የነበሩ ታሪኮች ክርስቶስ በእርሱ ያመኑትን በእርሱ አምነው የሞቱትን ኹሉ የሚያድናቸው ቸር እረኛ ስለመኾኑ እረኛው በጎቹን እንደተሸከመ አድርገው ይሥሉት ነበር፡፡ ሌላው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን እንዴት እንደተሳሳቱ ያሳሳታቸውን[78] ታሪክ የሚያሳይ እንዲኹም[79] በምሕላና በጸሎት ያለችን ነፍስ በኖኅ መርከብ አስመስለው ይሥሉ ነበር፡፡ የሐዲስ ኪዳን ታሪክም በተመሳሳይ መልኩ ይሣል ነበር፡፡ እንዲኹም ስንክሳር የድንግል ማርያምን ሥዕል በመጀመሪያ የሣለ ወንጌላዊው ሉቃስ እንደኾነ ይገልጻል[80]። የሥዕሎቹ አገልግሎት ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት እንዲኹም ስለ ሃይማኖቱ በሰማዕትነት የሞቱትን ወይም በሕይወት

---

[75] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ (ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948ዓ.ም)፣ ገጽ 673።
[76] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፀ. 25፥19፤ 37፥7፤ 1ኛ ነገ.6፥ 23፤ 2ኛ ነገ. 6፥2-7፣ ሕዝ. 9፥3፤ 10፥3፤ ሄኖክ 14፥11።
[77] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ 1ኛ ነገ. 7፥23-36።
[78] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፍ. 3፥1-7።
[79] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፍ. 7፥1-24።
[80] ስንክሳር ጥቅምት 22 የሚነበብ፡፡

ዘመናቸው በጸሎትና በመንፈሳዊ ትጋት ያሳለፉትን ጻድቃን ለማሰብ ነው፡፡ የሥዕሎቹ አሳሣል የሚሣሉበት ቦታ እና ቅርጽ የጌታ ስቅለት፣ የቅዱሳን፣ የመላእክት እየተባለ አቅጣጫቸው የቀለሙ አመራረጥና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ትኩረትና ጥንቃቄ ይደረግባቸዋል፡፡

ሥዕል እንዴት መሣል እንዳለበት የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ቀኖና ቢኖራትም፣ ያሉት ሥዕሎች ግን በአብዛኛው ሥርዓቱን የተከተሉ አይደሉም፡፡ እንዲያውም በቤተ-ክርስቲያኗ ቀኖና መሠረት የተሣለ ሥዕል የለም ለማለት ያስደፍራል፡፡ "...ሥዕሎቹ በፈረንጅ ፎቶግራፍ ተተክተው ይታያሉ፡፡ በቤተ-ክርስቲያናችን ሥርዓትም ይኹን ታሪክ የማይታወቀው የቅርፅ ምስል የቀለሙን ሥዕል ቦታ እያስለቀቀው ነው[81]።" በእንጦጦ ማርያም በቅርፅ የተቀረፀ ሥዕል ይገኛል፡፡ መረጃ ሰጪዎች የነበሩት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን "ቅርፅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክልክል ነው። ቅርፅ ራሱ ጣዖት ነው፡፡ ነገር ግን በትልልቅ አድባራት ጭምር ቅርፅ እናያለን።[82]

ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ የምንመለከታቸው ሥዕሎች የጥንቱን የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የአሳሣል ስልት የተከተሉ እንዳልኾኑና "በከተማው ሕዝብ እየተገዛ ለቤተ-ክርስቲያን የሚሰጠውና ከቤቱ የሚይዘው የላቲንን የግሪክን ኪነጥበብ የሚያሳዩና የሚመሰክሩ ሥዕሎችን ነው፡፡[83]

በመስቀል ላይ ሥዕል ሊሣል ይችላል፤ ነገር ግን ቅርፅ መቅረፅ አይቻልም፡፡ ኾኖም ከእነዚኽ ንዋያተ ቅድሳት ውጭ ለምሳሌ በመጐናፀፊያ፣ በጥላ የላይኛው ገጽ ላይ ተለጥፈው አንዳንዴ ሥዕለ ቅዱሳን ተሥለው ይታያሉ። በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በቀኖና መሠረት ሥዕለ ቅዱሳን በእነዚኽ ንዋያተ ቅድሳት ላይ እንዲሣሉ አልታዘዘም፡፡ ባልተለመደ ኹኔታ ሥዕለ ቅዱሳን የሚታዩባቸው ንዋያተ ቅድሳት መካከል በተለይ ጥላ(ድባብ) በአራቱም አብያተ ክርስቲያን ይገኛል።

## 3.7 የንዋያተ ቅድሳት ስያሜ፣ ምርትና ሥርጭት

በእያንዳንዱ ንዋያተ ቅድሳት ላይ ከምናየው ሃይማኖታዊ ፎክሎር በተጨማሪ የንዋየ ቅድሳትን ብያኔ፣ የማምረቻ ቦታና ከባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ የሚታየው ሃይማኖታዊ ፎክሎር እንደሚከተለው ቀርቧል።

[81] ሐመር መጽሄት (አስኳል አማረ)፣ "ንዋየ ቅድሳትን ለአገልግሎት ሊያውሏቸው ይገባልን?"፣ (ዐዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት1994)፣ ሐምሌ እና ነሐሴ ገጽ፡13።

[82] ለምሳሌ በአዲስ አበባ አራት ኪሎ ቅድስት ሥላሴ፣ ስድስት ኪሎ መንበረ ማርቆስ በአፀድ ውስጥ ቅርጾች አሉ። በተለይም ካቴድራል ሥላሴ ቤተ-ክርስቲያን የሕንጻው የውጭ ግድግዳ ላይ እንዲሁም በአጸድ ውስጥ በብዛት ይታያሉ፡፡

[83] መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 13 2000)፡፡

ንዋያተ ቅድሳት በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ቀኖና መሠረት፣ ኦርቶዶክሳዊ የአሳሣል ትውፊቱን ጠብቆ መሠራት ያለባቸው በቤተ-ክርስቲያኗ ባለሙያዎች መኾን መቻል ይኖርበታል፡፡ ማንኛውም ሰው መሥራት ስለሚችል ብቻ አይሠራቸውም፡፡ ኾኖም በተግባር በማን ይሠራሉ? ሲባል በአብዛኛው የሚሠሩት ሥራውን መሥራት በፈለገ እና መሥራት በቻለ ግለሰብ ወይም ተቋም ነው። ባለሙያው ቁሶቹን የሚሠራበት፣ ነጋዴው ለገበያ የሚያቀርብበት ዋናው ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት ነው። ስለዚኽ ሠሪውም ኾነ ሻጩ ዋና ጉዳዩ ገንዘብ ከኾነ ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን መጠበቅ አለመጠበቃቸው ገዢ እስካገኘ ድረስ ጉዳዩ ላይኾን ይችላል። ስለዚኽ ሠሪውም ኾነ ለገበያ አቅራቢው ገቢ እስካስገኘለት ድረስ ያመርታል። ይሸጣል። ማንም ያምርተው ወይም ይግዛው አገልግሎት የሚሰጡት ግን በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ነው። የንዋያተ ቅድሳት ገበያ ደግሞ ቤተ-ክርስቲያን እስካለች አለ። ምክንያቱም ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ያለ ንዋያተ ቅድሳት ቤተ-ክርስቲያን አይኾንም።

በየቤተ-ክርስቲያኑ "የንዋያተ ቅድሳት መሸጫ ሱቅ" ቢኖርም ኹሉንም ንዋያተ ቅድሳት የያዙ አይደሉም። ያሉትም ሱቆቹ ባሉበት ቤተ-ክርስቲያን ተመርተው ለሽያጭ የሚቀርቡ ሳይኾን ከነጋዴ ላይ የተገዙና ለትርፍ ተብለው የሚቀርቡ ናቸው፡፡

"የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻ እና መሸጫ ሱቅ" የሚለው ስያሜ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ንዋያተ ቅድሳት ለማለት ሙሴ በታዘዘው መሠረት "የቅብዐቱንም ዘይት ወስደኽ ማደሪያውን በእርሱም ያለውን ኹሉ ትቀባለህ እርሱንም ዕቃውንም ኹሉ ትቀድሳለህ ቅዱስ ይኾናል[84]፡፡" በተባለው መሠረት ከመቀደሳቸው በፊት ንዋየ ቅድሳት አይባሉም፡፡ ሱቅ ውስጥ የሚሸጡ ቅብዐ ቅዱስ ተቀብተው የከበሩና ተገቢው ጸሎት የተደረገላቸው ሳይኾኑ ገና ወደ ቤተ-ክርስቲያን ያልገቡ በመኾናቸው "ንዋያተ ቅድሳት" የሚለው ስያሜ ተገቢ አይደለም፡፡ "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" ከተባለ ደግሞ ንዋያተ ቅድሳት አይሸጡም፣ አይለወጡም፡፡ ስለዚኽ እንዴት ንዋያተ ቅድሳት ሊባሉ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ያስነሣል። "ቤተ-ክርስቲያኗ የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ አላት፤ ነገር ግን በቂ አይደሉም[85]፡፡"

ንዋያተ ቅድሳት የትኞቹን ያካትታሉ? የትኞቹንስ አያካትቱም? ለሚለው በተለይ የነገሥታት መገልገያ የነበሩና ለቤተ-ክርስቲያን የተሰጡ እንዲኹም በቤተ-ክርስቲያን ሙዝየም ውስጥ የሚገኙትን አንዳንዶቹ "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ "ንዋያተ ቅድሳት ሳይኾኑ ቅርስ ናቸው" በማለት በቅርስነት ብቻ ይፈርጇቸዋል፡፡ ለምሳሌ እንጦጦ ማርያም ሙዝየም ውስጥ ያሉ የነገሥታት መገልገያ የነበሩና ለነገሥታቱ የተለያዩ ሰዎች የተበረከቱ ዕቃዎች "ቅዱስ የሚያሰኛቸው ቅዱስ ቦታ

[84] ዘጸ. 40፥8።)

መገኘታቸው ካልኾነ ንዋያተ ቅድሳት ሊባሉ አይገባም።[86]" በሙዝየሙ ውስጥ ያሉ የነገሥታት ልብስ፣ የጦር መሣሪያ እንዲኹም የተለያዩ መገልገያዎችን በአስጎብኝዎች በሚደረግ ገለጻ "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" በማለት ለጎብኚዎች ይተዋወቃሉ፡፡ ከነገሥታት መገልገያ ለምሳሌ የንግሥና ልብስ፣ ዘውዶች እና መሰል መገልገያዎች ቅርስ እንጂ ንዋያተ ቅድሳት ሊባሉ እንደማይገባ መረጃ ሰጪ ሊቃውንት ይናገራሉ[87]፡፡ ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት በቡራኬና በቅብዐ ቅዱስ ከብረው ለአገልግሎት ተለይተው ያሉ የቤተ ክርስቲያን መገልገያዎችን መሆን መቻል አለበት፡፡ ከዚኽም ባሻገር በአገልግሎት የከበሩ ፓትሪያርኮች አልባሳት፣ ዘውድ፣ የጳጳሳት አስኬማ፣ የካህናቱ፣ የዲያቆናቱ…ልብሰ ተክህኖ ናቸው።

በሙዝየም ውስጥ ከሚገኙት መካከል ነገሥታቱ ለቤተ-ክርስቲያን በስጦታ የተሰጡት "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" በሚል ነው። ኾኖም ከእነዚኽ መካከል አንዳንዶቹ ሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያንን ያልጠበቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በእንጦጦ ማርያም ሙዝየም ከሚገኙ ሥዕሎች መካከል ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ለዓፄ ምኒልክ ከኢጣልያን መንግሥት የተላከ፣ በ1882 ከራሽያ ቤተ-ክርስቲያን ለአፄ ምኒልክ የተበረከተ "የድንግል ማርያም ቅርጽ" የሚል ነው፡፡ እነዚኽን ስንመለከት የቤተ-ክርስቲያኗን ቀኖና ያፋለሱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ቅርፅ እንደ ጣዖት ይቆጠራል፤ ጣዖት ደግሞ ቀኖናን ብቻ ሳይኾን ዶግማንም ያፋልሳል[88]፡፡ ቅርፅ ከመሠረቱ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊት የሚደግፈው ሃይማኖታዊ መገለጫ አይደለም፡፡

# 4 .ማጠቃለያና ይኹንታ

በጥናቱ የተገኘው ውጤት በቤተ-ክርስቲያን ግቢ (አጸድ) ውስጥ ያለ ነገር ኹሉ በጥቅል ስሙ ንዋያተ ቅድሳት ይባላል፡፡ ለሃይማኖታዊ ተግባር የሚውሉ የተለያዩ "ቁሳቁሶች" በሃይማኖቱ ሥርዓት መሠረት አገልግሎት ላይ ከዋሉ በኋላ ስማቸውም ኾነ ግብራቸው ተለውጦ ንዋያተ ቅድሳት የሚለውን ስያሜ ያገኛሉ። ቤተ-ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊዉን መሠረት እና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊቱን በመያዝ የሚሠሩትን ንዋያተ ቅድሳት በታዘዘው መሠረት እንዲሠሩና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ፤ በአገልግሎቱም ወቅት ማን መቼና እንዴት? መገልገል እንዳለበት ዝርዝር ሕግና ምሳሌያቸው ጭምር በጽሑፍ ሠፍሮ ይገኛል፡፡

[86] መረጃ ሰጭ፡- መምህር ቃለ ጽድቅ፣ እድሜ 71፣ (ቃለ-መጠይቅ ሚያዝያ 6 2000)፡፡

[87] መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 13 2000)፡፡

[88] መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 13 2000)፡፡

ኾኖም ኹሉም ንዋያተ ቅድሳት በተግባር በተጻፈው ሃይማኖታዊ ሕግ መሠረት የሚሠሩና አገልግሎት ላይ የሚውሉ አይደሉም። እነዚኽህ ተቃርኖዎች መታየታቸው የንዋያተ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያ ነው። በዝርዝር ጥናት ውስጥ እንደቀረበው ሃይማኖታዊ ፎክሎር የሚታይባቸው፤ አንደኛ "ንዋያተ ቅድሳት" የሚለው ስያሜ በተገቢው ቦታ አለመጠቀም። ለምሳሌ "የንዋያተ ቅድሳት መሸጫ ሱቅ"፣ ከዚኹ ጋር በተያያዘ ሌላው የንዋያተ ቅድሳቱ አምራች ከቤተክርስቲያን ውጭ መኾን፣ ኹለተኛ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ መለወጥ፣ የቅርፅ ለውጥ ጉልላትና በጣራው ክፈፍ ዙሪያ ይደረግ የነበረ ሻኩራ እንዲኹም ጉልላት እንዲቀር ማድረጉና የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ክፍሎች ወደ ኹለት እንዲቀንሱ እና ምሳሌያቸው አብሮ እንዲቀር አድርጓቸዋል። ሦስተኛው፤ ልብሰ ተክህኖ ሲኾን ይኸም የልብሱ ቀለም መለዋወጥ እና የአሰፋፍ ቅርፅ በአግባቡ አለመኾን ታይቶባቸዋል። አራተኛው የከበሮ ለዓለማዊ ዘፈን መዋል ነው። አምስተኛው ተቋመ ማኅቶት እንዲሠራ በታዘዘበት ሕግ በተግባር ሲሠራ አለመታየቱ ነው። ስድስተኛው ሥዕለ ቅዱሳን ሲኾን ይኸም በአዋቂዎች በምን መልክ መሣል እንዳለበት የተጻፈው ሕግ እንዳለ ኾኖ በተግባር ግን መለወጡ ነው። ሰባተኛው ጥላ(ድባብ) ሲኾን በጥላው ላይ የሚለጠፉ ቅዱሳት ሥዕላት ያለተገቢ ቦታቸው መገኘታቸው የሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያዎች ናቸው።

በአጠቃላይ ቤተ-ክርስቲያን የምትተዳደርበት ሕግ አንድ ኾኖ ሳለ በተለያዩ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የተጻፈውና የሚተገበረው የማይገናኝ ኾኖ በንዋየ ቅድሳቱ ላይ ይስተዋላል። ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ የተደነገጉ ሃይማኖታዊ ደንቦች በተግባር ካለው ጋር እንዳይፋለሱ የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች በአጥኚዋ ተጠቁሙዋል።

- ✓ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ለሃይማኖታዊ ተግባር የምትገለገልባቸው ቁሶቹ አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ሃይማኖታዊ እና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊታቸውን የጠበቁ ስለመኾናቸው ማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ ቢኖር፣
- ✓ ስለ ንዋየ ቅድሳት በጽሑፍ የሰፈሩ ደንቦች በተግባር ላለመዋላቸው ምክንያቶቹ በሰፊውና በዝርዝር ተጠንቶ ቢለይና መፍትሔ ቢሰጠው፣
- ✓ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻ ተቋማትን በስፋት ማቋቋም ብትችል የሚሉ ናቸው።

# ቅኔ ዘዝክረ አድዋ ወዘመነ ፋሽስት፡ ፍቺና ሐተታ

# (Qəne - Commemorating the Victory of Adwa and the Era of Fascist: Translation and Analysis)

ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው[89][90]

## ABSTRACT

This article is aimed at exploring how poem (ቅኔ) Scholars of Ethiopian Orthodox Tewahedo Church recoded and narrated the Italian invasion in general and the Victory of Adwa in particular in their Qəneyat (poems). To achieve this purpose, the researcher employed qualitative methodology with secondary sources (document analysis) as instruments of data collection. Findings of the study show that the Qəneyat were composed before and after the Battle of Adwa. The pre-Adwa Qəne yat are found to be prophetic and provoking in their message. The post-Adwa Qəneyat, whereas, praise our patriots fathers, mothers, and the king. In addition, the findings attest that the message depicted in the Qəneyat is quite similar with other historical books written on the event. This also assured that besides its spiritual value, Qəne can be used as a means of channel to transfer national values and histories from generation to generation.

*Keywords: Qəne, Victoy of Adwa, Italian invasion, Battle of Adwa, patriots*

[89] የአድዋ ድል በአልን 121ኛ ዓመት ለመዘከር የተዘጋጀ ጥናት፡፡

[90] ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው፣ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፊሎሎጂ (በግእዝ የጥንታዊ ጽሑፎች ጥናት) 3ኛ ዲግሪ ምሩቅና በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ አስተማሪ፡፡

# መግቢያ

የመላ አፍሪካ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ባንዴራ የኾነው የአድዋ ድል በዓል 121ኛ ዓመቱን በማስቆጠር ላይ ይገኛል። ታሪክ እንደሚዘክረው ነጮች መላ አፍሪካን ሲወሩ አፍሪካም አንገቷን ለነጮች የባርነት ቀንበር ዝቅ ስታደርግ ይኽንን ኢሰብአዊ ድርጊት በመቃወምና ለቅኝ ገዥዎች ባለመንበርከክ ሉዓላዊነቷን አስከብራ የኖረች ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ መኾኗ የታወቀ ነው። ምንም እንኳ ፋሽስት ኢጣልያ በዘመናዊ መሣሪያውና በሠለጠነ ወታደራዊ ኀይል በመመካት ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ ለማጥቃት ቢሞክርም አልተሳካለትም። ይኹን እንጅ የኢትዮጵያ ነጻነት በልጆቿ አጥንትና ደም ላይ የተገነባ መኾኑን ማስተዋል ያሻል።

በዚኽ የነጻነት ጉዞ ኹሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግምባር ቀደም ተሰላፊ በመኾን ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ድርሻዋን ተወጥታለች። ቀሳውስቱና ካህናቱ በጾምና በጸሎት እግዚአብሔርን በመለመን ሠራዊቱንም በማበረታታት ከጦር ሜዳ አልተለዩም። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስም መስቀላቸውን በእጃቸው ይዘው የኢትዮጵያን ወታደሮች ለትግል እያደፋፈሩ በጦርነቱ ላይ መሳተፋቸውን ታሪክ ያስረዳል[91]። ከድል በኋላም ንጉሠ ነገሥቱ ዓጼ ምኒልክና ሠራዊታቸው በአኵሱም ካቴድራል በሥርዓተ ቅዳሴና በዝማሬ ለእግዜአብሔር ምስጋና በማቅረብ ደስታቸውን ገልጸዋል።[92] ይኽም ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዚኽ ሀገራዊ ድሉ መገኘት የነበራትን አስተዋጽኦ በግልጽ ያመለክታል።

ኢትዮጵያውያን በአድዋ ጦርነት በጣልያን ላይ የተቀዳጁት ድል ለመላ አፈሪካውያን ከነጭ ቅኝ ተገዥነትና ከባርነት መውጣት እንደሚችሉ በተግባር ያረጋገጠ ምሳሌ በመኾን ያገለገለ የነጻነት ደወል ነው። በአፍሪካውያን የጦርነት ታሪክ ውስጥ ከተከበሩና ከተደነቁ ጦርነቶች መካከል አንዱ ኢትዮጵያውያን አውሮፓውያንን ድል የነሡበት የአድዋ ጦርነት መኾኑ በታሪክ ይታወቃል[93]። ሃይማኖት ቋንቋ ጾታ እድሜ ሳይገድባቸው መላ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት[94] የድል አድራጊዎችና

[91] አንደርዜይ ባርትኒስኪ እና ዮዓና ማንቴል-ኒዮችኮ፣(ዓለማየሁ አበበ፣ተርጓሚ)፣የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁኑ ዘመን (2005፣350)።

[92] ዝኒ ከማሁ (2005፣ 352)

[93] ጳውሎስ ኞኞ፣አጤ ምኒልክ፣(ማንኩሳ አሳታሚ ድርጅት፣ 1984፣217)።

[94] ዝኒ ከማሁ

የአሸናፊዎች በዓል ሊከበር የሚገባው በአባት አርበኞችና በቤተ ክርስቲያን መድረክ ብቻ ሳይኾን በወጣቱና በሁሉም ማኅበረሰብ፤ ከዚኽም አልፎ የጥቁር ሕዝብ ድል በመኾኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን በመላ አፍሪካ ጭምር በዓሉ ከፍ ብሎ መታሰብ እንዳለበት ማሰብ ተገቢ ነው።

ለሀገራችን ለልዕልናችን ለሰብእናችን ደማቸውን ላፈሰሱት አጥንታቸውን ለከሰከሱት አባቶቻችንና እናቶቻችን የመታሰቢያ ሻማ እያበራን ልንዘክራቸው ይጋባል። የነበራቸውን የሀገር ፍቅርና የአንድነት መንፈስ በማሰብ ማድነቅ፤ የአርበኝነት ታሪካቸውን እያነበብን የመወያያ አጀንዳዎቻችን ማድረግ ያስፈልጋል። አርበኞች አባቶቻችንና እናቶቻችን መኳንንቱ መሳፍንቱ ከጦርነቱ በፊት የነበሩትን ወራትና ቀናት በምን መልኩ እና ምን እየተወያዩ አሳለፏቸው? ወደጦር ሜዳ ሲዘምቱስ ምን እያሉ ይፎክሩና ያቅራሩ ነበር? በምን ዓይነት ሥነ-ልቦና ዘመቱ? ድል አድርገው ከተመለሱ በኋላ የነበሩትን ቀናትና ወራትስ እንዴት አሳለፏቸው? በጦር ሜዳ ለተሰዋው ምን ዓይነት መታሰቢያ አደረጉ? የአርበኞቹን ቤተሰቦች በምን መልኩ አጽናኗቸው? በጦርነቱ የቆሰለው አርበኛስ በምን መልኩ ቁስሉ ታከመ? ከአርበኞቹ በኋላ የተነሣው ትውልድስ ስለእነርሱ ምን አለ? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሡ በመወያየት ይኽንን ታሪካዊና የነጻነት በዓል ማሰብና ማክበር ታሪካዊ ግዴታችን ነው። ይኽ ጥናት በዚኽ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥረቶች ምሳሌ ኾኖ ሊያገለግል ይችላል።

ለዚኽ ጽሑፍ ግባት የሚኾኑ ቅኔዎች የተሰበሰቡት ከታለያዩ የቅኔ መዛግብትና ቤተ መዘክር ነው። ይዘታቸውም በፋሽት ኢጣሊያ ተዳጋጋሚ ወረራና በኢትዮጵያውያን አርበኞች የነጻነት ትግል ላይ ያተኮረ ነው። ቅኔዎቹ ከይዘታቸው አንጻር ቅድመ አድዋና ድኅረ አድዋ ተብለው ተፈርጀዋል። የመረጃ ትንተናው ሂደትም የግእዙን ቅኔ ፍቺ (ትርጉም) በአማርኛ በማስቀመጥ[95] በቅኔው ውስጥ በሰምና ወርቅ እንዲኾም በምሳሌ የተገለጠውን ሐሳብ በመዘርዘር ነው። በቅኔዎቹ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች በታሪክ መጻሕፍት ከተመዘገቡ እውነታዎች ጋር በማዛመድና በማነጻጸር ባለቅኔው ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልእክት የጽሑፉ አዘጋጅ ተንትኗል።

[95] በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ቅኔዎች የተተረጎሙት ጽንሰ ሀሳብን መሠረት በማድረግ ነው፤ ቀጥተኛና ቃል በቃል ትርጉምን መሠረት አያደርግም

ይኽን ጥናት በተፈለገው መጠንና ጥራት ለማጠናቀቅ እንዳይቻል የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙ ሲሆን ከነዚኽም ውስጥ፡-

- በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት አንዳንዶቹ ቅኔዎች ደራሲያቸው (ባለቅኔው) ባለመታወቁና ቅኔዎቹ የተደሩሱበት ዘመን (ዓመት) አለማታወቁ ቅኔዎቹን በዘመን ቅደም-ተከተል ማስቀመጥ አልተቻለም፡፡
- በጊዜና በገንዘብ ውስንነት ምክንያት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ትኩረት የሚያ ደርጉ በርካታ ቅኔዎችን መሰብሰብ ባለመቻሉ በጥናቱ ውስጥ ለናሙናነት የተካተቱት ቅኔዎች ቁጥር አናሳ ኾኗል፡፡

# ከአድዋ ጦርነት በፊት የተደረጉ ቅኔዎች

አስቀድሞ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፋሽስት ጣሊያን ጋር ባደገረችው ጦርነት ኹሉ አልተለየችም፡፡ ቀሳውስቱና ካህናቱ በጾምና በጸሎት ከማገዝ ባሻገር በእጃቸው የጦር መሣሪያ ይዘው ከጠላት ጋር ለመፋለም ቁርጥ ኀሊና እንደነበራቸው የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

ተምሮ ተምሮ ካልሰበሰቡት
እንዴት ያሳዝናል ሲባክን ዕውቀት፡፡

ሂጂ ተመለሽ ግቢ አገርሽ ቅኔ
ወንዶች ከዋሉበት መዋሌ ነው እኔ፡፡[96]

እያሉ የዘረጉትን ጉባዔ ሳይቀር አጥፈው ከጠላት ጋር ለመፋለም ወደ ሰልፉ ይወጡ ነበር፡፡ ቅድመ አድዋ ቅኔዎች ጦርነቱ በኢትዮጵያውያን ድል አድራጊነት እንደሚጠናቀቅ የሚጠቁሙ ትንቢታዊ ቅኔዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ቀድመው አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያነቃቁ (የሚያበረታቱ) ናቸው፡፡ ቅኔዎቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል[97]፡፡

---

[96] ይህ ግጥም አለቃ መርሻ ወልደ ማርያም የተባሉ የቅኔ ምሁር የገጠሙት ሲኾን እርሳቸውም ሽምግልና ሳይገድባቸው በ70 ዘመናቸው ከፋሺስት ጣሊያን ጋር በመዋጋት ብዙዎችን ገድለው ለጀግኖች የሚገባውን የሞት ጽዋ መቀበላቸውን ታሪክ ይዘክራል፡፡ (አስረስ የኔሰው፣ *ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?*፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1951፣91)፡፡

[97] በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱት አብዛኞዎቹ ቅኔዎች (አንዳንዶቹ ከነትርጉማቸው) የተወሰዱት

**ቅኔ**

ምኒልክ ግበር ላዕለ ሮምያ መጠነ እዴከ ትክል፣
አምጣነ ለአጺድ በጽሐ ማዕረራ ወመዋዕሊሃ ለንጉል፣

ዓዲ ተዘከር ውስተ ወንጌል፣
ላዕለ ሮምያ በለስ ኢሀሎ አስካል፣
ከመ ይቤ ወልደ ያሬድ ቃል።

**ትርጉም**

ምኒልክ፣ በሮምያ ላይ እጅህ እንደቻለ መጠን አድርግ
መከሯ ለመታጨድ ዘመኗም ለጥፋት

ቀርቧልና።

ዳግመኛም በወንጌል ያለውን አስብ፣ በሮምያ በለስ ላይ ፍሬ የለም፣
እንዳለ ወልደ ያሬድ /ቃል (ወልድ)።

ይኽ ቅኔ አሠረ ነጋሢ በመባል የሚታወቅ የእዝል ዕጣነ ሞገር[98] ቅኔ ነው። ቅኔው የተነገረውም ከአድዋ ጦርነት በፊት በ1883 ዓ.ም የሐምሌ ሚካኤል አዲስ አበባ አለቃ ለማ ኀይሉ በተባሉ ሊቅ[99] ነው።

ዓፄ ምኒልክ በወቅቱ የጠላታቸው ጠላት (ዓፄ ዮሐንስ) ከጣሊያን ጋር የተወዳጁና ስምም የነበሩ ቢኾንም[100] ባለቅኔው ወዳጅነታቸው እንደማይዘልቅና ሮማውያን በዓፄ ምኒልክና በሠራዊታቸው እጅ እንደ መከር አዝመራ እንደሚታጨዱ በትንቢታዊ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ተዘጋጅቶ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያሳተመው የግእዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ ኹለተኛና ሦስተኛ ቅጾች ነው። በቅኔዎቹ ግርጌ ማስታወሻ የተወሰዱበት ቅጽና ገጽ ተገልጧል።

[98] ዕጣነ ሞገር ከቅኔ አርእስት (ስያሜዎች) አንዱ ነው። ከጉባዔ ቃና ጀምሮ ያሉ ቅኔዎች የሚጠሩባቸው የራሳቸው ስሞች አሏቸው። የተለያዩ ጸሐፍት በተለያየ መንገድ ስለሚቆጥሯቸው የቅኔ አርእስትን ብዛት አንዳንዶች 22 ሲያደርጉት ሌሎች ደግሞ 17 አድርግው ጽፈዋል። ለምሳሌ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ 22 ናቸው ሲሉ ይኸውም የሃያ ኹለቱ አርእስተ ድኀ፤ የ22 ሥነ-ፍጥረታት ምሳሌ እንደኾኑ አትተዋል። ማርየ ይግዛው ደግሞ በዋናነት 9 መኾናቸውን በመግለጽ በዝርዝር ሲቆጠሩ ደግሞ 17 መኾናቸውን ሀብተ ማርያም ወርቅነህን እና የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚን ዋቢ በማድረግ ጽፏል። የአርእስቱ ስያሜ አመጣጥና እንዲኹም ምሳሌያዊ ትርጉሙ የተለያየ መኾኑን ለመረዳት ከላይ የተገለጹት ጸሐፍት የዘገቡትን ይመለከቷል።

[99] ማርየ ይግዛው፣ ቅኔያዊ የእውቀት ፈጠራ፣ የጀርመን ባህል ማእከል፣ 2006።

[100] 10ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ 1984 ገጽ 138።

ቅኔያቸው አመልክተዋል፡፡ ሊቁ ለቅኔያችው መነሻ ያደረጉት ክርስቶስ በወንጌል ፍሬ የማትሰጥ በለስ እንደምትቆረጥ ያስተማረውን ነው (ሉቃ ፲፫፡፯)፡፡ ሮምን ፍሬ (መልካም ነገር) በማይገኝባት በለስ መስለው መቆረጫዋም (መውደቂያዋም) ተቃርቧልና ብትወጋት ድል ታደርጋለኽ በማለት ንጉሡን በቅኔያቸው መክረዋል፡፡ ቅኔው የማነቃቂያ ቅስቀሳ ነው፡፡ ይኽንን የጦርነት ቀስቃሺና ትንቢታዊ ቅኔ የሰሙ ብዙ ሰዎች በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ጦርነት መነሣቱ እንደማይቀር ገመቱ፡፡ ቅኔው በተነገረ በአምስተኛ ዓመቱ የአድዋው ጦርነት ተንሥቶ ንጉሡ የጣሊያንን ጦር እንደተመከሩት ድል አድርገዋል፡፡ ይኽም ቅኔ ከምሥጢሩ ባሻገር ስለ ባለቅኔው ማንነት ስናስብ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በእውቀት ብቻ ሳይሆን በጾምና በጸሎት ሕይወታቸው የታነጸ ስለነበር አንዳንዶቹ መጻእያትን/ ወደፊት የሚኾኑትን ነገሮች የማወቅ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ያመለክታል፡፡

**ቅኔ**[101]

በሕፅነ ምኒልክ ይረፍቅ ሰማዕተ ልዕልና

ወበሕፅነ ሰማዕት ይትሃወስ አሠረ ምኒልክ ላእከ እስመ እምሮምያ ፈተተ አድባረ ድንጋዔ ወሐውክ ምኒልክ ንጉሠ አድኅኖ ዘኢዮር መልአክ

ወእግረ ምኒልክ ኢይትሐወክ

እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔ ፍኖት ወልደ አምላክ

ቡርክትሂ ገነተ ጽጌ እስመ ውእቱ ቡሩክ

በስመ ምኒልክ ቀዳማዊ ዘይመጽእ ምኒልክ ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ

በጽባሕ እስመ አቅረበ ሙስና ሮምያ

መሥዋዕተ ሠርከ

**ትርጉም**

የልዕልና ሰማዕት በምኒልክ ጭን (ጎን) ይቀመጣል፡፡

በሰማዕት ጭንም (ጎንም) የንጉሥ

---

[101] መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መዘክር፣ አዲስ አበባ፡፡

ምኒልክ ምልክት ይንቀሳቀሳል፡፡

የድንጋጤና የሁከት ተራሮችን ከሮም ቆራርሷልና

የማዳን ንጉሥ ምኒልክ የኢዮር

መልአክ ነው፡፡

የምኒልክ እግር አይታወክም፤

መንገድን የሚያቀና ወልደ አምላክ በፊቱ ይሄዳልና፡፡

ገነተ ጽጌም የተባረከች ናት፤

በቀዳማዊ ምኒልክ ስም የሚመጣ ዳግማዊ ምኒልክ የተባረከ ነውና፡፡

ሶርያም ለእርሱ ትሰግዳለች፤ ትንበረከካለች፤

የሮም ጥፋት (መደምሰስ) መሥዋዕተ ሠርክን

በማለዳ አቅርቧልና፡፡

ይህ መወድስ ቅኔ ይባላል፡፡ የቤተ መዘክሩ አስጎብኝ እንደገለጹት የቅኔው ባለቤት መልአከ ገነት ጽጌ የሚባሉ ሊቅ ናቸው፡፡ ቅኔውን የተቀኙት ከአድዋው ጦርነት ቀደም ብለው ነው፡፡ የቅኔው ዋና ምሥጢር ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በከበረ ሰማዕት (ቅዱስ ጊዮርጊስ) ተራዳኢነት ልባቸው በትዕቢት እንደ ተራራ የገዘፈ ፋሽስት ጣሊያኖችን በአድዋ ጦርነት ድል ማድረጋቸውን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ዓፄ ምኒልክ ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ኢትዮጵያን ከጠላት ወረራ በመታደጋቸው ባለቅኔው ንጉሠ አድኅኖ (የማዳን ንጉሥ) ዘኢዮር መልአክ (የኢዮር[102] መልአክ) በማለት ያሞግሳል፡፡ እንዲኹም ባለ ቅኔው ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወልደ አምላክ ክርስቶስ መንገዳቸውን (ሥራቸውን) የሚያከናውንላቸው መኾኑን ስለሚያምኑ እግረ ልቡናቸው ከአድዋ ጦርነት ወደኋላ እንደማይልና ልባቸው እንደማይታወክ ገልጠዋል፡፡ ይኽንንም እውነታ ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ በሚለው መጽሐፉ አንዳንድ ሰዎች የጣልያንን ገናናነት ለምኒልክ በመንገርና ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀ ጣሊያን ሠራዊት ጋር ለመግጠም እንደማይቻል ወሬ ሲያናፍሱ ንጉሠ ነገሥቱ መኳንንቱን ሰብስበው በአንደበታቸው

[102] የመላእክት ከተማ

የተናገሩትን በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ “… አንፍራ! እኔ እንደኾንሁ መዝመቴን አልተውምና ስለኢጣሊያ ዘመናዊ መሣሪያና ገናናነት አትንገሩኝ፡፡ ኃይል የእግዚአብሔር ነውና እጋጠማለሁ፡፡ ብትዘምቱም ብትቀሩም ሬሳየን ከጦር ሜዳ ፈልጉት …”[103]፡፡ በተጨማሪም በዚሁ መጽሐፍ ዓፄ ምኒልክ ለራስ ወልደ ጊዮርጊስና ለደጃዝማች ተሰማ ያስተላለፉት መመሪያ እንዲኽ የሚል ነበር “… ከእኔ ጋር ያለው ሠራዊት ብዙ ነው፡፡ ልክና መጠን የለውም፡፡ እግዚአብሔር ካልተለየን በትግሬ በኩል ላለው ጦር ይበቃል፤ እናንተም ወደ አውሳ ዝመቱ”[104] ብለዋል፡፡ እነዚኽ ጥቅሶች የሚያስረዱን ከላይ ባለቅኔው እንደተናገረው ንጉሠ ነገሥቱ በኃይለ እግዚአ ብሔር የሚታመኑና ከድንጋጤና ከሁከት የራቁ መኾናቸውን የሚያሳይ ነው[105]፡፡

የቅኔው ኹለተኛ ክፍል ምሥጢር ደግሞ “በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው” (ሉቃ. 19፥38) የሚለውን የወንጌል ቃል መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ድርሰቱ በቀዳማዊ ምኒልክ ስም የመጣውን ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያን የተባረከ ነው በማለት ያወድሳል፡፡

በመቀጠልም ከቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮ ውስጥ “መሥዋዕተ ነግህ መሥዋዕተ ሠርክ”[106] የሚለውን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ባለቅኔው በሠርክ መሥዋዕት የተመሰለ የሮማውያን ድምሳሴ መኾኑን ይገልጻል፡፡ “ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ በማለዳ መሥዋዕት አቅርቧልና ሶርያ ትሰግድለታለች ትንበረከክለታለች” የሚለው ኃይለ ቃል የሚያስረዳን በአድዋ ጦርነት ጊዜ የጣሊያን ሠራዊት በኢትዮጵያውያን አርበኞች እጅ የካቲት 23 ከንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እንደ መሥዋዕት በግ አንገቱን መቀላቱንና ሥጋው መቆራረጡን ያሳያል፡፡

በመጨራሻም ባለቅኔው “ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ /ሶርያም ትሰግድ ለታለች ትንበረከክለታለች” በማለት በትንቢታዊ ቅኔያቸው የገለጹት የታሪክ እውነታ ነው፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ ኞኞ[107] እንደገለጡት በአድዋ ድል ጊዜ በመላው ዓለም ያሉ

[103] ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣1984፣165፡፡

[104] ዝኒ ከማሁ፣ 1984፡167፡፡

[105] አበው “ባልና ሚስት ካንድ ወንዝ ይቀዳሉ” እንዲሉ የንጉሠ ነገሥቱ ባለቤት እቴጌ ጣይቱም ደፋርና ልበ ሙሉ በመኾናቸው ኮንት አንቶኔሊ የኢጣሊያ መንግሥት መልእክተኛ የውጫሌውን ውል በጦር ኃይል እንደሚያስከብር በዛቻ መናገሩን ሲሰሙ “የዛሬ ሳምንት አድርገው፡፡ በዚኽ የሚደነግጥልህ የለም፡፡ ሂድ የፎከርክበትን አድርግ፡፡ እኛም የመጣውን እናነሣዋለን፡፡ እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው በዚኽ የሌለ አይምሰልህ፡፡ የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ ነው እንጅ ሞት አይባልም፡፡ አሁንም ሂድ፤ አይምሽብህ፤ የፎከርክበትን በፈቀደህ ጊዜ አድርገው እኛም ከዚኽ እንቆይሃለን” በማለት ነበር የተናገሩት፡፡ (ዝኒ ከማሁ ፣148)

[106] ጧትና ማታ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የምስጋና መሥዋዕት

[107] ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣1984፣217-19፡፡

ጋዜጦች በመጀመሪያ ገጻቸው የምኒልክንና የጣይቱን ፎቶ ግራፍ በማውጣት የድሉን ዜና ለመላው ዓለም አሰምተዋል፡፡ ይኽንን የድል አድራጊዎች ዜና የሰማው ሕዝብ ሁሉ በፈረንሳይ በጀርመን በሩሲያና በአሜሪካ ታላላቅ ሕዝባዊ የደስታ ስብሰባዎች ማድረጉ የታሪክ ሐቅ ነው፡፡ “ እንኳን ደስ አለዎት” የሚሉ የተለያዩ ደብዳቤዎች ከዓለም ዙሪያ ካሉ መሪዎች እንደተላኩላቸውና አንዳንዶቹም የምኒልክን መልክ ለማየት ከመጓጓታቸው የተነሣ ለደብዳቤዎቻቸው መልስ እንዲጻፍላቸውና የምኒልክ መልክ ያረፈበት የኢተዮጵያ ቴምብር ተለጥፎ በፖስታ ቤት እንዲላክላቸው መጠየቃቸው ታውቋል፡፡ ጳውሎስ ኞኞ እንደሚያስረዱት ከኹሉም በላይ ከአውስትራሊያና ከቤኑዚላ የተጻፉት ደብዳቤዎች “የእርስዎ ወታደሮች መኾን እንፈልጋለን” የሚሉ ጥያቄዎችን የያዙ ነበሩ፡፡ ይኽም የትንቢታዊውን ቅኔ እውን መሆን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ ባለቅኔው በመወድሱ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ እንደገለጸው አጤ ምኒልክ በእግዚአብሔር ቸርነት እንዲሁም በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ መሪነትና ተራዳኢነት የሚተማመኑ መሆናቸውን ለማጠየቅ በራሳቸውና በሠራዊታቸው ኹሉ እጅ ባለው ሰይፍ “የምኒልክ ተስፋው እግዚአብሔር ነው”፣ “ቅዱስ ጊዮርጊስ” የሚለው ተጽፎ መገኘቱ የሚቀጥለው ሥዕል ምስክር ነው፡፡




**ሥዕል ፩፡- ዳግማዊ አፄ ምኒልክ**



2ሥዕል ፪፡- የቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የተጻፈበት ሰይፍ

(source:https://tse2.mm.bing.net/th?id=OIP.aa2C_gmpdfEjgZPOenDjLwHaDl&pid=15.1&P=0&w=318&h=155)

## ከአድዋ ድል በኋላ የተደረሱ ቅኔዎችና ምሥጢራዊ ትርጉም

የቅኔ ሊቃውንት የተለያዩ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ ተፈጥሯዊና የመሳሰሉ ክስተቶችን ለቅኔ ዘረፋቸው (ድርሰታቸው) መነሻ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ ጥልቅና ረቂቅ ምሥጢርን ባዘለ ቅኔያቸው የአድዋን ድልና ተያያዥ ጉዳዮችን ሲያመሠጥሩት ኑረዋል፤ አሁንም ያመሠጥሩታል፡፡ ወደፊትም ታሪክንና የቅኔን ጥበብ የተካኑ ሊቃውንት እስካሉ ድረስ ይኽ ታሪካዊ የአድዋ ድል በቅኔ ጥበብ ሲዘከር ይኖራል፡፡ በዚኽ ክፍለ ርእስ ሥር ለናሙናነት የተካተቱት ቅኔዎች ከአድዋ ድል ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ገጽታዎችን ያንፀባርቃሉ፡፡ ለማስረጃ የሚከተሉትን ቅኔዎች እንመለከታለን፡፡

| ቅኔ[18] | ትርጉም |
| --- | --- |
| ፩ ሙሴ ፋሽስት ግብረ ማኅበር ይዜኑ | ሙሴ ፋሽስት የማኅበር ሥራን ያወራል፣ |
| ጽዋዐ እብሬት ይትወከፍ በዐለ ሰሙን አኮኑ፡፡ | የተራ ፅዋን ይቀበል ዘንድ ባለ ሳምንት ነውና፡፡ |

ይኽ ቅኔ የግእዝ ጉባኤ ቃና ሲኾን ባለ ቅኔው ለሐሳባቸው መነሻ ያደረጉት የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ሥርዐት መሠረት ምእመናን በየሳምንቱ እሑድ ወይም በወር ውስጥ ከሚውሉት ቅዱሳን በዓላት መካከል አንዱን መርጠው በመሰባሰብ፣ ማኅበር (አንድነት) መሥርተው መንፈሳዊ ጽዋ ይጠጣሉ፡፡ የማኅበሩ ሰብሳቢ ሙሴ[108] ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ኀላፊነቱም ማኅበሩን መምራትና የሚቀጥለው ሳምንት (ወር) ተረኛ ማን እንደሆነ በማሳወቅ ጽዋውን እንዲቀበል ማድረግ ነው፡፡ በዚህ አንጻር ፋሽስት ጣሊያንን በሙሴ በመመሰል ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያውያንን በግፍ ከጨፈጨፈ በኋላ የዕልቂቱን ጽዋ በተራው መቀበሉን፣ የሽንፈት ጽዋ መጎንጨቱን አመሥጥረዋል፡፡

**ቅኔ** (*አሠረ ንጉሥ*)[109]

በወርኀ ምኒልክ ሰላም ዘአግበርክሙ
መጥባሕተክሙ ማኅረሰ
ኵናተ ሐራ ግበሩ ይእዜ ማዕጸደክሙ ሐዲሰ
ማእረሩ ለዔሳው እምድኅረ የብሰ
ሐመልማለ ገመል ኢያውፅእ ወጽጌ ፈረሰ
በአትልዎ ዘነበ ወርእሰ፡፡

**ትርጉም**

በምኒልክ ሰላም ወራት ሾተላችሁን ማረሻ
ያሠራችሁ (የሠራችሁ)፤
አዲስ ማጭዳችሁን የወታደሮች

108 ሙሴ ተብሎ መሰየሙ በኦሪት ዘመን የነበረው ነቢዩ ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን በአንድነት መርቶ ባሕረ ኤርትራን አሻግሮ ሕገ እግዚአብሔርን እያስተማረ ከአምልኮ ጣኦት ወደ አምልኮ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኀጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንደመለሳቸው ኹሉ እርሱም ቃለ እግዚአብሔርን እያስተማረ፣ የታመሙትን እየጠየቀ፣ የተጣሉትን እያስታረቀ፣ የተቸገሩት እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ እያመቻቸ የማኅበሩ አባላት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ልዕልና እንዲኖራቸው ለማገዝ የተመረጠ በመሆኑ ሙሴ ተብሎ ተሰይሟል፡፡

109 የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ 2ኛ ቅጽ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ 1984፣112፡፡

ጦር አድርጉ፡፡

የዔሳው አዝመራ ከደረቀ በኋላ

ገመል ልምላሜን፣ አበባ ፈረስንም

እንዳያወጣ

ጅራትንና ራስን በማስከተል፡፡

ይኽ ቅኔ የእዝል እጣነ ሞገር ቅኔ ሲሆን በተለየ ስሙ አሠረ ንጉሥ በመባል ይታወቃል፡፡ የቅኔው ዋና ጭብጥ ጦርነት በሌለበትና ሰላም በሰፈነበት ዘመን ሾተልን (ሰይፍን፣ ጋሻን ወዘተ) ማረሻ ማሠራት እንደተለመደ ኹሉ፤ በጠብ ዘመን ደግሞ ማጭድን ወይም ማረሻን ወደ ጋሻና ጦር ቀይሮ ለማሠራት የሚያስመኝ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በዚኽም መሠረት ባለቅኔው ዓፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ድል ከነሱ በኋላ አርሶ አደሩ ያለ አንዳች ጦርነት በሰላም እያረሰ መኖሩን በማስታወስ አሁን ግን ጣልያኖች የአድዋን በቀል ለመበቀል ለጦርነት መንቀሳቀስ ሊጀምሩ እንደሚችሉ በመጠቆም አርሶ አደሩ ያለ አገር ነጻነት ማረስና ማዝመር ስለማይችል ወደአርበኝነት ተግባር እንዲንቀሳቀስ ባለቅኔው ያሳስባሉ፡፡ አዝመራ ከደረቀ በኋላ እንደማያለመልምና እንደማያብብ ቢታወቅም የዔሳውም (የአረቦችም ጠብ) ደጀንና ፊታውራሪን በማከታተል የግመልን በቀልና[110] በፈረስ የሚካሄድ ጦርነትን እንዳያመጣ በመስጋት ባለቅኔው በዘመናቸው የነበሩትን ኢትዮጵያውያንን በቅኔያቸው አስጠንቅቀዋል፡፡ በበቀለኛነቱ በግመል የተመሰለው ጣሊያን በአድዋ ጦርነት የሽንፈትን የሞት ጽዋን ቀምሶ ከተመለሰ በኋላ ለብዙ ዓመታት ሲዘጋጅ ቆይቶ ኢትጵያን በድጋሜ ለመውረር መነሣቱ ሊቁ በቅኔያቸው የገለጹት ሥጋት እንዳልቀረ ያስረዳል፡፡

**ቅኔ**[111]

፫ ምኒልክ ኢበልዓ ኀፍረተ ቀትል

እምነ ይሁዳ ዘተርፈ

ወበበትረ እድ ዘኮነት ለከንቱ ዘባነ ፀሩ

ቀሠፈ

[110] የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት የግመልን በቀለኛነት እንዲህ በማለት ይገልጡታል "ግመል በቀለኛ ናት፤ አጥብቆ የመታትን እስከ ስድስትና ሰባት ዓመት አትዘነጋም፤ ባጥ ብላ (ዘልላ) ትረግጠዋለች ስፍራ ሲመቻት ገደል ገፍታ ትጥለዋለች" (ማቴ.3፥4)፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣1988፡፡

[111] የግእዝ ቅኔያት፣ ሁለተኛ ቅጽ፣1984፣381፡፡

እስመ ፀር ስመ ዘተሳተፈ
ትምክህተ ሰናክሬም ቄጽለ ጊዜ ነግህ ተዐጽፈ
ወበሠርክ ፍሬሁ ተነግፈ።

**ትርጉም**

የይሁዳ ትራፊ የሆነ የጦር ጎፍረትን
ምኒልክ አልበላም፤
ለከንቱ በሾነች የእጁ በትርም (ሰይፍ)
የጠላቱን ጀርባ ገረፈ (ቆረጠ)
በስም የተሳተፈ (አንድ የሆነ ጠላት)
የሰናክሬም ትምክህት ቅጠልን በነግህ ጊዜ
ተጎናጽፏልና፤
በምሽትም ፍሬው ረግፏልና።

የዚኽ ቅኔ ዋናው መልእክትም በባህል ላይ በተመረኮዘ ምሳሌና በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው። በባህላችን አንድ በማዕረግም ሆነ በዕድሜ አነስተኛ የሆነ ሰው ያስተረፈውን ፍርፋሪ (ምግብ) ከእርሱ የሚልቅ ሰው አይበላውም። በታሪክ ደግሞ ይሁዳ (ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ የነበረው) ጦረኛ (ወታደር) እንደነበረና አባቱንና እናቱን ማርኮ አሳፋሪ ተግባር እንደፈጸመ ይታወቃል[112]። ባለ ቅኔው የይሁዳን ጦርነት ከአድዋው ጦርነት ጋር በማነጻጸር ዓፄ ምኒልክን የጦርነት ትራፊን አልበላም (በጦርነቱ ድል አልሆነም) በማለት ያመሠጥራል። ይልቁንም የአህያ ጀርባ በበትር እንደሚመታ ዓፄ ምኒልክም የጠላታቸውን የጣሊያንን ጀርባ በእጃቸው (በሠራዊታቸው) እጅ ላይ ባለች በትር (ሰይፍ) ቆራረጡት ይላል። በተጨማሪም በንቀትና በትዕቢት በይሁዳው ንጉሥ በሕዝቅያስ ላይ ሲዘብት የነበረውን የአሦርን ንጉሥ ሰናክሬምን በእግዚአብሔር ቸርነት ሕዝቅያስ ድል እንዳደረገው[113] እንዲሁም ገና ሳይዋጋ "… በቅርብ ቀን ምኒልክን በቀፎ ውስጥ አስሬ ሮማ አመጣዋለሁ…"[114] በማለት በሮም አደባባይ ጉራውን ሲቸረችር የነበረውን የጀኔራል ባራቲየሪን ሠራዊት በኃይለ እግዚአብሔር የሚመካው ዓፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ላይ ጧት ታይቶ ማታ እንደሚረግፍ ጤዛ እንዳረገፈው ባለቅኔው ገልጸዋል።

---

112 አባቱን ሰልቦ ገድሏል፤ እናቱንም በግብር አውቋታል። (የማርቆስ ወንጌል አንድምታ ትርጓሜ "…ወምስሌሆሙ ጉልቊ ዝኩ ዘፍጥረቱ ክርዳድ … ይሁዳ ዘአግብአ" የሚለውን ተመልከት።

113 ነገሥት 19፥35

114 ጳውሎስ ኞኞ፣አጤ ምኒልክ፣1984፡163።

**ቅኔ**[115]

ሰላም አልብነ ምስለ ሰብአ ሮሜ ወለሰብአ
ሮሜ ምስሌነ ኢሀለዎሙ ሰላም
ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመደ ሥጋ ወአጽም
እስመ ከተረነ ደምከ ቀለም።
ኦ ዘትሠይም
ቀስተ ሕይወታ ለነፍስ በደመና
ገቦ ንዝሀተ ደም
አንተሰ ታስተዴሉ በውስተ ዛቲ ዓለም
ኪያሆሙ ለጥኢና ወኪያነ ለሕማም
ወእንዘ እምጥንትነ ጴጥሮስ በተዓድዎ ሕግ ፍጹም
ለዘተፃብዐከ ንፃብዖ ወዘተቃወመከ
ንትቃወሞ።

**ትርጉም**

የአጥንትና የሥጋ ዘመድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ
ከሮም ሰዎች ጋር ሰላም የለንም።
ለሮም ሰዎችም ከእኛ ጋር ሰላም የላቸውም
ደምህ ቀለም ከትሮናልና (ለይቶናልና)። የነፍስ የሕይወቷ በጎን/ ደመና የደም ርጭት የምትሸም አንተ ነህ፤
አንተ ግን በዚህች ዓለም እነርሱን
ለጤንነት፣ እኛን ለሕማም ታዘጋጃለህ።
ከጥንታችን /ጴጥሮስ ጀምረን ፍጹም
ሕግን በመተላለፍ
የተጣላህን እንጣላዋለን፣የተቃወመህንም
እንቃወማለን።

የዚኽ ቅኔ ምሥጢር መሠረት ያደረገው ባህልን ነው። ይኸውም አንዱ የአንዱን ወንድም በመግደሉ ምክንያት በደም የተለያዩ ሰዎች በማንኛውም ማኅበራዊ ጉዳይ አይገናኙም። ባለ ቅኔው በዚኽ ባህላዊ እውነታ ላይ ተመሥርተው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ባፈሰሰው ደም ላይ በተመሠረተው እምነት (ሃይማኖት) የሮማ ካህናትና

[115] አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ መጽሐፈ ቅኔ ዝክረ ሊቃውንት፣ 1963፡718።

የኢትዮጵያ ካህናት አይተባበሩም፣ አንድ አይደሉም፡፡ ከዚኽም የተነሣ የሮም ካቶሊክና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አብረው አይቀድሱም፤ በአንድነት አይቆርቡም፡፡ ዳግመኛም ዓለምን በጥፋት ውኃ እንዳያጠፋት ቀስትን በደመና/ ቀስተ ደመና (የቃል ኪዳን ምልክት) አምላክ እንዳደረገ፣ የሰዎችን የነፍስ መዳንም በደሙ ፈሳሽነት አደረገ፡፡

በክርስቶስ ኹለት ባሕርይ ሁለት ፈቃድ  በማለት የሃይማኖትን እውነተኛ መንገድ የለወጡ የሮም ካህናት ተቃዋሚዎች ሲሆኑ (በመቃወማቸው)፣ ኢትዮጵያውያን ለሥጋዊ መከራ ተዳረጉ፡፡ ይኽም ማለት ሃይማኖትን የሚለውጥና የሚያጠፉ ፋሽስትን በመዋጋት ኢትዮጵያውያን ብዙ መከራ የደረሰባቸው መኾኑን ያስገነዝባል፡፡ ጠቅለል ባለ አገላለጽ፣ ሮማውያን (ጣልያኖች) ግዛትን የማስፋፋት ፍትወታቸውን ለመፈጸም ይረዳቸው ዘንድ፣ የሮም ካህናት ሃይማኖትን እንሰብካለን በማለት በሃይማኖት ሰበብ ያደረጉት ሙከራ የስለላ ተግባር[116] መኾኑን የተረዱት ባለቅኔው "ሰላም አልብነ ምስለ ሰብአ ሮሜ፤ ከሮም ሰዎች ጋር ሰላም የለንም" በማለት አመሥጥረውታል፡፡

**ቅኔ**

አልብየ ምት ብሂሎትኪ ኢትዮጵያ
እሙን ወኢይትሔሰው ቃልኪ ለመርዓዊ
ሕግ እስከ ምጽአቱ
ምትኪ አምጣነ ኢኮነ ዘሀሎ ምስሌኪ[117]

**ትርጉም**

ኢትዮጵያ ሆይ፣ ባል የለኝም ማለትሽ
የታመነ ነው፤ ቃልሽም አይታበልም፡፡
እስከ ሕግ ሙሽራው መምጣት ድረስ
ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አልሆነምና፡፡

ይኽ ቅኔ ሕንጼሃ ወይንም ሣህልከ ይባላል፡፡ ባለ ቅኔው የተጠቀሙት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳምራዊቷን ሴት ባነጋገራት ጊዜ  "ሂጅና ባልሽን ጥሪው"  ቢላት እርሷም "ባል የለኝም" አለችው፡፡ ጌታም መልሶ "ባል የለኝም ማለትሽ እውነት ነው አምስት ባሎች ነበሩሽና፡፡ አሁን

[116] አስረስ የኔሰው፣ትቤ አክሡም መኑ አንተ? 1951፡2፡፡
[117] የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ 3ኛ ቅጽ፣1995፡194፡፡

ግን ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም"[118] አላት። ባለ ቅኔው ይኽን የወንጌል ቃል ምሳሌ በማድረግ ኢትዮጵያ በአምስቱ የኢጣልያ ወረራ ዓመታት መሪ እንዳልነበራት ለጊዜው ኢትዮጵያን እገዛለሁ ይል የነበረው ግፈኛው ፋሽስትም መሪዋ አለመሆኑን ከማመሥጠራቸው ጋር፣ የራስዋ መሪ እንደሚመለስና ፋሽስት ኢጣልያም የኢትዮጵያ ገዥ ሆኖ እንደማይቀጥል ተንብየዋል። ከዚኽም መረዳት ያለብን ሌላው ጉዳይ ባለቅኔው ንጉሥንና ሀገርን በባልና ሚስት የመመሰላቸው ምሥጢር ነው። ይኸውም ባልና ሚስት በመተማመንና በመፈቃቀር ላይ የተመሠረተ ትዳር ከሌላቸው ትዳራቸው ሊጸና ጎጇቸው ይቀናል ተብሎ አይታሰብም። ልጅ ወልደው በምግባር በሃይማኖት አንጸው ማሳደግ አይችሉም። ቤታቸው ኹል ጊዜ እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ወይም እንደ እሳት የሚያቃጥል ድባብ ይሰፍንበታል። ከዚኽም አልፎ ባል በኀይልና በጉልበት ሚስትን አስገድዶ ለመግዛት ቢሞክር አይሳካለተም፤ መጠፋፋትንም ሊያስከትል ይችላል። እንዲኹም መንግሥት (ንጉሥ) እና ሀገር (ሕዝብ) በመተማመንና በመደማመጥ ካልኾነ ምንም ዓይነት መልካም ውጤት ማስመዝገብ አይቻሉም። መንግሥት የሚያወጣቸው ሕጎችና ደንቦች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም። ከዚኽም የተነሣ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል በየጊዜው በሚደረጉ ፍጥጫዎች የብዙ ሰዎች ደም ይፈስሳል። በተቃራኒው ባልና ሚስት አንድነታቸውን በመተማመንና በመግባባት ላይ የመሠረቱ እንደኾነ አንድነታቸው ይጸናል፤ትዳራቸው ይቀናል፤ ሀብታቸው ይበዛል፤ ጎረቤት ዘመድ አዝማድ ምሳሌ ያደርጋቸዋል። እንዲኹም መንግሥትና ሕዝብ ልብ ለልብ ተናቦ በመወያየትና ችግሮችን በጋራ በመፍታት የሚጓዝ ከኾነ ሀገር ትለማለች፤ ሰብአዊ መብት ይከበራል፤ ኹሉም እንደሚገባው የድርሻውን ያገኛል።

## ቅኔ

አልቦ እምሕዝብ ዘአጠየቀነ
ከመ እምአይቴ ምጽአቱ ወኀበ አይቴ ነገዱ
ለዘእምርትቅ መጽአ ያርብኃ ገዳም አሐዱ
ፍጹመ እስመ ይመስሎ ለሉቃስ በእዱ
ወካዕበ ይመስል
ዮሐንስሃ ነቢየ እምነ ርእሱ እስከ ክሳዱ
አስይፍትሂ ኀለይተ ሞት እለ ተአንገዱ
በቅድመ ባዕል ያርብሃዊ በክሣድ ይወርዱ

[118] ዮሐ 4፥1-18

አኮኑ ውእቱ ለያርብሓዊ መፍቅዱ
ሥጋሁ ከመ ይብልኡ ባዕዳኒሁ ምስለ
አዝማዱ።

**ትርጉም**

ከሩቅ የመጣ አንዱን የዱር አርበኛ
አመጣጡ ከየት ነገዱም ከወዴት እንደኾነ
ከሕዝብ ያስረዳ የለም።
ሉቃስን በእጁ ይመስለዋልና፤
ዳግመኛም ከራሱ እስከ አንገቱ
ነቢዩ ዮሐንስን ይመስላል።
እንግዶች የሆኑ የሞት ዘፋኞች /ሰይፎችም
በባለጸጋ አርበኛ ፊት በአንገት ይወርዳሉ።
ባዕዳኑ ከዘመዶቹ ጋር ሥጋውን ይበሉት ዘንድ ለአርበኛ ፈቃዱ ነውና።

እንግዳ ሰው "ሲታይ ከየት መጣህ" "የማን ወገን ነህ" "ከራስ ቅልህ ከፊት አወራረድህ እገሌን ከእጂህ አካባቢ እግሌትመስላለህ"ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል። እንዲሁም ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት በዱር በገደል በዋሻ በፍርኩታ ወድቆ ይገኝ የነበረው ኢትዮጵያዊ አርበኛ በእጁ ሉቃስን በራሱና በአንገቱ ዮሐንስን ይመስላል፤ ማለትም አርበኛው እንደ ሉቃስ እጁን፣ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ አንገቱን መቆረጡንና በስም ይኽ እገሌ ነው ያ እገሌ ነው ተብሎ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን ባለቅኔው ያስረዳሉ። ይኽም ፋሽስት ኢጣልጣን በወገኖቻችን ላይ ያደረሰው መከራና ግፍ ምን ያኽል አሰቃቂ እንደነበር ከዚኽ ቅኔ መረዳት እንችላለን።

በቅኔው ኹለተኛ ክፍል አዝማሪዎች በባለጸጋ ፊት እስክስታ በአንገት እንደሚወርዱ፣ ሰይፎችም (ጎራዴዎች) በአርበኛ ፊት በአንገት ይወርዳሉ ማለት አርበኛው በፋሽስት ጎራዴ አንገቱ እየታረደ ሥጋው እየተቀረደደ መገደሉ ተመስጥሯል። ባዕዳኑ ከዘመዶቹ ጋር ሥጋውን ይበሉ ዘንድ ለአርበኛ ፈቃዱ ነውና ማለትም ባዕዳን የተባሉ ፋሽስት ኢጣልያን ዘመድ ከተባሉ ኢትዮጵያውያን ባንዳዎች ጋር አርበኛውን ለመውጋት ቢተባበሩም አርበኛው ወደኋላ ሳያፈገፍግ አንገቱን ለሰይፍ ደረቱን ለጦር ለመስጠት ፈቃደኛ ኾነ በማለት ሊቁ ያመሠጥራሉ።

ምኒልክ ከብካብ የዓለም
መጀመሪያ ኢትዮጵያ እምከ
ዘኢታፈቅር ደመኛ ከጥቁር ጋራ
ነጩን አቅርባልን ነበር ለእኛ

እኛም ብናየው በየጊዜው፣
ይሻላል ከነጩ
የወትሮው መናኛ፤
ጣልያን ጋለሞታ
ጋግራዋለችና ነጩን ወፍራም አድርጋ
ክፉኛ፣ አመትከዊ ምድረ ትግራይ
የማትገዛ ለዳኛ፣ የጸነሰችውን ሰብአ
ሮሜ አስወረደችው ለተኛ፡፡ ማእከለ
መትረየስ ወመድፍ ላእካነ ንጉሥ
ሰልፈኛ በደም አይቷታልና ጎራዴህ ክፉ
ቁራኛ፡፡[119]

ከላይ ያለው መወድስ ቅኔ ምንም እንኳ ፍርንዱስ (ግእዝና አማርኛ) ቢሆንም በውስጡ የያዛቸው ሐሳቦች ግን ትንታኔ የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ ከብካብ ማለት ሠርግ ሲሆን ሠርግ ደግሞ በዚህ ዓለም የማኅበራዊ ኑሮ መጀመሪያ ነው፡፡ ማለትም አንድ ሰው ትዳር ከመሠረተ በኋላ በአካባቢው ያለው ማኅበረሰብ ጋር በሚተዳደርበት ሕግና ደንብ መገዛት ይጀምራል፤ ለምሳሌ በእድርና በመሳሰሉ ነገሮች ይሳተፋል፡፡ በዚኽ ምሳሌ መሠረት ከብካብ በተባሉ ዓፄ ምኒልክ አማካኝነት ኢትዮጵያ ከዓለም ሥላጣኔ ተቋዳሽ መኾኗን ቅኔው ያመሠጥራል፡፡ አሁንም ባለቅኔው በነጭ ጤፍና በጥቁር ጤፍ ማንጸሪያነት ጣሊያናዊውን እና ኢትዮጵያዊውን አስተዳደር እያነጻጸሩ የጥቁር ጤፍ እንጀራ ከነጭ ጤፍ እንጀራ የተሻለ ጥቅም እንዳለው ኹሉ እንዲኹም ሲያዩት የሚያምር ከሚመስለው ነገር ግን ጥቅም ከሌለው ከነጩ ጤፍ (ጣሊያናዊ ቅኝ ገዥ) መናኛ/የማይረባ የሚመስለው ጥቁሩ ጤፍ (ኢትዮጵያዊ መሪ) እንደሚሻል ቅኔው በምሥጢር ያስረዳል፡፡ ከመጠን በላይ ወፍራም ሆኖ የተጋገረ እንጀራ ለመብላት እንደማይመረጥ ኹሉ ጋለሞታ የተባለች ጣልያን ዜጎቿን ልበ ወፍራም/ ደንዳናና ጨካኝ አድርጋ ጋግራቸዋለችና ማለት አሳድጋቸዋለችና ለአገዛዝ አይመቹም እያለ ነው፡፡

በመጨረሻም ዓይነ ወግ ክፉ ቁራኛ/ ሾተላይ የርጉዝ ሴት ፅንስን እንደሚያስወርድ፣ የምኒልክ ጎራዴም የኢጣልያንን ሠራዊት እንደውርጃ እየበጣጠሰ ከትግራይ ምድር ማስወጣቱን ቅኔው ያስረዳል፡፡ አንድም የምኒልክ ፓለቲካዊ ተቃዋሚ የነበረው ራስ መንገሻ በአድዋ ጦርነት ምክንያት ለጊዜው ከምኒልክ ጋር በመተባበር ለድሉ መሠረታዊ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢኾንም በኋላ ግን 80ሺህ ጦር አሰልፎ

[119]የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ 3ኛ ቅጽ፣1995፣135፡፡

የምኒልክን ንጉሠ ነገሥትነት እንደማይቀበል አስታውቆ ነበር። ይኹን እንጂ ዓፄ ምኒልክ በራስ መኰንን የሚመራ 40ሺህ ጦር ሲያዘምቱበት ገና ወሳኙ ግጥሚያ ሳይደረግ የመንገሻ ሠራዊት መፍረክረክ መጀመሩን ታሪክ ያስረዳል።[120]

## ማጠቃለያና አስተያየት

ከላይ በተጠቀሱት ቅኔዎች ውስጥ እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዕውቀታቸው ጥልቅ አእምሯቸው ምጡቅ ከመሆኑ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀታቸውን በሃያማኖታዊ አስተምህሮ ብቻ ሳይገድቡት ወቅታዊ ጉዳዮችንም ለመተንተን እንደአስፈላጊነቱ በምሳሌነት እንደ ተጠቀሙበት ያሳያል። ሊቃውንቱ ሐሳቦቻቸውንም ሲያቀርቡ ምክንያታዊ (Logical) የሆኑ ማስረጃዎችን በማቅረብ በመኾኑ የአድማጮቻቸውን ልቡና የመግዛትና የመማረክ አቅማቸው እጅግ ከፍተኛ መኾኑንም ከቅኔዎቻቸው እንገነዘባለን። በቅኔዎቹ ውስጥ የተንጸባረቀውና ልናስተውለው የሚገባን ሌላው ወሳኝ ጉዳይ፣ ፋሽስት ጣልያን ሀገራችንን በተደጋጋሚ ሲወር አርበኞች አባቶቻችን ሰይፍ መዝዘው ጦር ሰብቀው ጠላትን ለመመከት ሲዋጉ፤ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መንፈሳውያን አባቶቻችን ደግሞ ከጸሎታቸው ባሻገር በቅኔያቸው ነገሥታቱና አርበኞቹ አስቀድመው እንዲዘጋጁ የማስጠንቀቅና የማነቃቃት ሥራን በመሥራት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ተወጥተዋል። በተጨማሪም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንነቱ እንዲኮራና ለነጻነቱ አስፈላጊውን መሥዋዕትነት እንዲከፍል ዋጋ ከሌለው ነጭ ጤፍ (ፋሽስት) ይልቅ ዋጋ ያለው ጥቁር ጤፍ (ኢትዮጵያዊ መሪ) ይሻልሃል፤ እውነተኛ ባሏ (ንጉሧ) እስኪመለስ ድረስ ኢትዮጵያ ትጠብቃለች፤ … እያሉ የአርበኛውንና የሕዝቡን ሥነ ልቡና በማነቃቃትና በማበረታታት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ከኹሉም በላይ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን ለአፍሪካ በሙሉ የነጻነት እንቅስቃሴ መሠረት የሆነውን ድል ያጎናጸፉን አባቶቻችን የከፈሉትን መሥዋዕትነት ለማወቅ እንችል ዘንድ ዘመን ተሻጋሪ በሆኑ ቅኔዎቻቸው ለአሁኑም ኾነ ለወደፊቱ ትውልድ የሚበቃ የታሪክ ገጸ በረከት አውርሰውናል።

በመጨረሻም በዚኽ ጥናት ውስጥ በናሙናነት ከተካተቱት በቁጥር ጥቂት ከኾኑ

[120] አንደርዜይ ባርትኒስኪ እና ዮዓና ማንቴል-ኒዮችኮ፣(ዓለማየሁ አበበ፣ተርጓሚ)፣የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁኑ ዘመን (2005፣429)

ቅኔዎች ከላይ ያለውን ጠቋሚ መረጃን ማግኘት ከተቻለ በተነሣው ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ተጨማሪ ቅኔዎችን መሰብሰብና ማጥናት ቢቻል ላቅ ያለና ሚዛን የሚደፋ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል መገመት አይከብድም። በመኾኑም በዚኽ ጥናት በተዳሰሰውም ኾነ በሌሎች ተዛማጅ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሊሎች አጥኚዎች ትኩረት እንዲያደርጉበት የዚኽ ጥናት ባለቤት መጠቆም ይወዳል።